# ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በተለይም ከንጉሥ ሰለሞን ንጉሥነት ቀጥሎ ባሉት ዘመናት ስለታቦቱ በየትም ሥፍራ የሚናገር ክፍል አይገኝም ። ንጉሥ ሰለሞን ከእግዚአብሔር በተቀበለው ትዕዛዝ መሠረት ለታቦቱ ማደሪያ የእሥራኤልን ቤተ መቅደስ ካሠራና ታቦቱ በዚያ ሥፍራ ከተቀመጠ በኋላ በአንድም ሥፍራ ላይ ሲጠቀስ አናገኘውም ። ታቦቱ እንደዚህ ፥ ያለ ምንም መግለጫ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መሰወሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማራማሪዎችንና በአይሁድ ታሪክ ላይ ጥናት የሚያካሂዱትን ግራ ያጋባ ሁኔታ ሆኖአል ። ለዚህ ችግር መፍትሔ ሆኖ የተገኘው በኢትዮጵያውያን ዘንድ በሚገኘው እና "ክብረ ነገሥት" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ታሪክ ነው ።

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ታላቅ ክብር ያለው ሲሆን ፥ እንዲያውም በዓፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት መጽሐፉ በእንግሊዛውያን እጅ ይገኝ ስለነበር ለእንግሊዝ መንግሥት "የኢትዮጵያን ሕግጋት የያዘ ክብረ ነገሥት የተሰኘ መጽሐፍ በእናንተ ዘንድ አለ ። እባካችሁ በማን እጅ እንደሚገኝ ፈልጋችሁ ላኩልኝ ። ያለ እዚህ መጽሐፍ የአገሬ ሕዝብ አይታዘዝልኝም የሚል መልዕክት ልከው እአአ በታህሣሥ 14 1872 መጽሐፉ ለዓፄ ዮሐንስ እንደተመለሰላቸው የታሪክ ማህደር ይዘግባል ።

ክብረ ነገሥት መቼ እንደተፃፈ በእርግጥ ለማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም ይህንና እንደዚሁም በርካታ ሌሎች ጽሑፎችን ወደ እንግሊዘኛ የተረጎሙት ፥ ሰር ኢ ኤ ዋሊስ ቡድጅ "ንግሥት ሳባና አንዲያ ልጇ ምኒልክ" በተሰኘው መጽሐፋቸው ታሪኩ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የቆየ ሊሆን ቢችልም ክብረ ነገሥት የተፃፈው ወይም የተቀናበረው በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ እንደሆነ ይዘግባሉ። በተጨማሪም አቀናባሪው የግብጽ (ቆብጥ) ቄስ እንደነበረ እና በመጀመሪያ በቆብጥ ቋንቋ እንደተጻፈ ይናገራሉ ። ከዚያም ጽሑፉ በንጉሥ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት ወደ አረብኛ እንደተተረጎመ ፥ ከአረብኛም ይስሐቅ በተባለ ሰው ወደ ግዕዝ እንደተተረጎመ ይናገራሉ ።

"የቃል ኪዳኑ ታቦት" በሚል ርዕስ መጽሐፋቸውን ያሳተሙት ገሪስሰን እና ሙንሮ-ሄይ ግን በስድስተኛው ክፍለ ዘመን

ተጻፈ ለማለት ያስቸግራል ይላሉ ። ይልቅስ ጽሑፉ የተቀነባበረው በዓፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ነው ። ለዚህ አቋማቸው የሚያቀርቡት ነጥቦች ፤

- በጽሑፉ የንጉሥ ካሌብ ሥም ብቻ መጠቀሱ ፥
- ጽሑፉ ስለ ክርስቲያኖች የበላይነት የሚናገር በመሆኑ ድንገትም በዓፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት በአረቢያ በተከሄደው ጦርነት የክርስቲያን ወገን የሆነው የዓፄ ካሌብ ጦር አሸናፊ ስለበር፥
- እንደገናም በጽሑፉ የሮም መንግሥት በዓለም ታላቅነት ያለው ሆኖ ቀርቧል ፤ በዓፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ይህ እውነተኛ ክስተት ነበር ።

ክብረ ነገሥት 117 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ፥ ስለ ንግሥት ሳባ እና ስለ ንጉሥ ሰለሞን ታሪክ ፥ ስለ ልጃቸው ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ እንደዚሁም የታቦቱን አመጣጥ በተመለከተ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በተጨማሪ ከብዙ በጥቂቱ ስለ ቃዬል እና ስለ አቤል ታሪክ ፤ ስለኖኅና ስለ ውሃው ሙላት እንደዚሁም እግዚአብሔር ስለገባለት ቃል ኪዳን ፤ ስለ አብራሃም ታሪክ ፤ ስለኢትዮጵያና ስለሮም መንግሥት ፤ ስለክርስቶስ ምጽዓት ወዘተ.... ይገኙበታል ። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ንጉሥ ሰለሞንና ስለ ንግሥት ሳባ ታሪክ ከክብረ ነገሥት በተለየ ሁኔታ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችም ይገኛሉ ።

በክብረ ነገሥት ላይ የሰፈረው የንግሥት ሳባ እና የታቦቱ አመጣጥ ታሪክ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው ። ንጉሥ ሰለሞን አባቱን ንጉሥ ዳዊትን ተክቶ በዙፋን በተቀመጠ ጊዜ (ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው እግዚአብሔር ጥበበኛ አደርጎት ነበርና) ዝናው በዓለም ሁሉ ተሰማ ። በተለይም ቤተ መቅደሱን ለማሠራት እንዲቻለው ለሕንፃው ማሠሪያ የሚሆኑ ዕቃዎችን እንዲያመጡለት ለታወቁ ነጋዴዎች በሙሉ መልዕክት ልኮ ነበርና እነዚህ ነጋዴዎች ኢየሩሳሌም በሄዱ ጊዜ የንጉሡን ጥበብ አይተው ይገረሙና ይደነቁ ነበር ። ከነዚህም ነጋዴዎች አንዱ ታምሪን የተሰኘ ኢትዮጵያዊ ነበርና ይህ ነጋዴ የንጉሥ ሰለሞንን ዝና ይዞ ለንግሥት ሳባ ይነግራታል ።

ንግሥቲቷ እራሷ ጥበብን የምትሻ ነበረችና ይህንን ባለዝና ለማየት ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ግመሎች ፥ በቅሎዎችና አህዮች አስጭና ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ታደርጋለች ። ኢየሩሳሌም በደረሰች ጊዜ ንጉሥ ሰለሞን በታላቅ ክብር ተቀብሏት አስተናገዳት ። በየጊዜውም እየተገናኙ ይነጋገሩ ነበር ። በዚህም ወቅት ንግሥቲቷ

በአገሯ ፀሐይን እንደሚያመልኩ ፤ አንዳንዶችም ድንጋይ ፥ እንጨት ፥ ዛፍ ፥ የተቀረጸ ምስል እንደሚያመልኩ ታጫውተዋለች ፤ እርሱ ደግሞ የዓለምን ፈጣሪ እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ እንደሚገባ ያስረዳታል ። እርሷም ከዚህ ጊዜ በኋላ ፀሐይን እንደማታመልክና የእሥራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን እንደምታመልክ የቃል ኪዳኑም ታቦት ለእርሷ ለዘሯና ለመንግሥቷ በሙሉ "እመቤቷ" እንደምትሆን ቃል ትገባለች ። (የቃልኪዳኑ ታቦት በክብረ ነገሥት የሚጠቀሰው በእንስት ጾታ ነው) ።

ከስድስት ወር ቆይታ በኋላም ንግሥት ሳባ ወደ አገሯ ለመመለስ ተነሳች ። ንጉሥ ሰለሞንም እግዚአብሔር ከእርሷ ልጅ ይሰጠው እንደሆነ አሰበና ከእርሷ ጋር ለመተኛት አሰበ ። ራት ግብዣም አዘጋጀላትና ምግቡ ጨው፥ ቅመማ ቅመም እንደዚሁም ኾምጣጤ በዝቶበት እንዲሠራ አዘዘ ። ራቱም ተበልቶ ካበቃና እንግዶቹ ከሄዱ በኋላ ፥ ንጉሡ ከእርሱ ጋር እንድትተኛ ጠየቃት ። እርሷ ግን በግድ ያለፈቃዱ አንድም ነገር እንዳያደርጋት ቃል እንዲገባላት አስደረገችው ። እርሱም እንደዚሁ ያለፈቃዱ ከቤተ መንግሥቱ አንድም ነገር እንዳትወስድ ቃል አስገባትና ወደ የመኝታቸው ገቡ ። ሌሊት የበላችው ምግብ ጨዋማ ስለነበር ውኃ ይጠማትና ተነስታ ንጉሡን ብትመለከት ዓይኑን ጨፍኖ ስለነበር የተኛ መስሏት ቀስ ብላ በክፍሉ ውስጥ ከተቀመጠው ውኃ ለመጠጣት ስትል ንጉሡ እጇን ይዞ የገባሽውን ውል አፍርሰሻልና እኔም በገባሁት ቃል አልያዝም ብሎ ይረታታል ። አብረውም ይተኛሉ ።

የዛን ጊዜም ንጉሥ ሰለሞን አንድ ሕልም ያያል ። ሕልሙም በጣም የምታበራ ፀሐይ ከሰማይ ወርዳ በታለቅ ብርሃን በእሥራኤል ላይ ታበራለች ። ከዚያም በድንገት ወደ ኢትዮጵያ ተጉዛ በዚያ ከበፊቱ በሚበልጥ ብርሃን ስታበራና ያም ደግሞ ለዘላለም እንደሆነ ተመለከተ ። ንጉሡም ፀሐይዋ ትመለስ እንደሆነ ለማየት ጠበቀ ነገር ግን ሳትመለስ ቀረች ። ንጉሥ ሰለሞን ከእንቅልፉ በተነሳ ጊዜ በጣም ተረበሸ ።

ከዚያም ንግሥት ሳባን ያሰናብታታል ። ከጣቱ ቀለበት አውልቆም "ማስታወሻ እንዲሆንሽ ይህችን ቀለበት ውሰጂ ፤ ድንገትም ከአንቺ ዘር ካገኘሁና ወንድ ልጅ ከሆነ ይህ ለምልክት ይሆናል ወደ እኔም ይመለሳል ። ዛሬ ሌሊት በሕልሜ ታላቅ የፀሓይ ብርሃን ከእሥራኤል ወደ ኢትዮጵያ ሲሄድ አይቻለሁና ድንገትም ይህች አገር በአንቺ ሳትባረክ አትቀርም" ብሏት አሰናበታት ።

ንግሥት ሳባም ከዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በኋላ ወንድ ልጅ

ወለደች ። ስሙንም "ቤይን ሌህኬም" ወይም ምኒልክ ብላ ጠራችው ፥ ትርጓሜውም "የጥበበኛው ልጅ" ማለት ነው ። (አህመድ አልሐፍኒ አልቂናኢ የተባሉ ጸሐፊ ከ97 ዓመት በፊት "አልጀዋህር አልሒሳን ፊታሪክ አልሐበሻን" በተሰኘ መጽሐፋቸው ምኒልክ የሚለው ሥያሜ የአረቢኛ ቃል እንደሆነ ትርጓሜውም - ሚኒ ወ ላይኪ በአማርኛም ከእኔ ለአንቺ ለማለት እንደነበር ይዘግባሉ ።) ምንሊክም የ22 ዓመት ዕድሜ ሲሞላው አባቱን ለማየት በጣም አድርጎ እናቱን ያስጨንቅ ነበርና ወደ ንጉሥ ሰለሞን ትልከዋለች ። ምንልክም ጋዛ በተሰኘች ፥ንጉሥ ሰለሞን ለእናቱ በሰጣት ከተማ በደረሰ ጊዜ ታለቅ አቀባበል ተደረገለት ። ልጁም አባቱን በጣም ይመስል ስለነበር ብዙዎችም ይህ ንጉሥ ሰለሞን ነው ይሉ ነበር ፤ አንዳንዶች ደግሞ ንጉሡ ቤተ መንግሥቱን በኢየሩሳሌም እያሠራ ነው ይሉ ነበር ።

ሕዝቡም ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ለንጉሥ ሰለሞን የሆነውን በነገሩት ጊዜ በቶሎ ወደ እርሱ ይዘውት እንዲያመጡት አዘዛቸው ። ልጁንም ባየ ጊዜ በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ ሊሾመው ፈለገ ። ምኒልክ ግን አሻፈረኝ አለ ። ብዙ ጊዜ ሞክሮ ስላቃተው ንጉሥ ሰለሞን ልጁን ምንሊክን በኢትዮጵያ ላይ ንጉሥ አድርጎ ሾመው ፤ ስሙም ንጉሥ ዳዊት ሁለተኛ ተባለ ።

ከልጁ ጋርም አብሮ የሚሄዱ ከእሥራኤል ወገን ከካህናቶችም ወገን የበኩር ልጆች እንዲላኩ ተወሰነ ። ምኒልክም በኢትዮጵያ ላይ ንጉሥ ሆኖ ስለተቀባ በከተማዋ ታላቅ ደስታ ሆነ ፤ በሰዎችም ሁሉ ዘንድ ። ነገር ግን ከእሥራኤል ወገን ከንጉሡ ጋር ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ በተመረጡት ዘንድ ሐዘን ሆነ ። ሐዘናቸውም የቃል ኪዳኑን ታቦት ትተው ሊሄዱ ስለሆነ ነበር ።

"በእርግጥ እመቤታችንና ተስፋችን ናት ፥ የምንመካባትም ናት፥ በእረፏም በበረከቷም አድገናል ። እንዴት አሁን ጽዮንን ትተን ለመሄድ ይቻለናል ። ምክንያቱም ለእርሷ ተሰጥተናልና ። ምን እናድርግ? እምቢ ብንልና ንጉሡን ብንቃወም እንገደላለን ፤ የአባቶቻችንና የንጉሡን ትዕዛዝ ለመተላለፍ አንችልም ። ስለዚህ ጽዮንን (ታቦቱን) በተመለከተ ምን እናድርግ ?" ተባባሉ ።

የሊቀ ካህኑ የዛዶቅ ልጅ አዛሪያ ከወገኖቹ ጋር ታቦቱን ከመቅደሱ ለመስረቅና ወደ ኢትዮጵያ ከእነርሱ ጋር ለመውሰድ በሚስጥር ተማከረ ። ሁሉም ገንዘብ አዋጡና በታቦቱ ቅርጽ እንጨት አሠሩ ። ከዚያም አዛሪያ ተኝቶ እያለ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦለት እንዴት አድርጎ ታቦቱን ከቤተ መቅደሱ እንደሚያወጣው

ነገረው ። በተነገረውም መሠረት አዛሪያ ሌሎች ሦስት ሰዎች እና ያዘጋጁትን እንጨት ይዘው ወደ መቅደሱ ገቡ ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ረድቶአቸው ከመቅጽፈት የእግዚአብሔርን ሕግ ማደሪያ ይዘው ወደ አዛሪያ ቤት ተመለሱ ። ታቦቱም በዚያ ለሰባት ቀንና ለሰባት ሌሊት በዚያ ቆየ ።

ሰለሞንም ልጁን ምኒልክን ባረከ ፤ ሕዝቡም በታላቅ ሐዘን ለምንሊክ አሸኛኘት አደረጉለት በጣምም እያለቀሱ ሸኙዋቸው ። ሕዝቡ የሚያለቅሰው የንጉሡ ልጅና የእስራኤል የበኩር ልጆች በመሄዳቸው ነበር ሳያውቁት ግን ያለቅሱ የነበሩት ለታቦቱ ነበር ። ሰለሞንም ከቤተ መንግሥቱ ሆኖ ሲመለከት የባለጉዞዎቹን ግርማ አይቶ ልቡም ደነገጠ ። "ወዮ ለእኔ! ግርማዬ ከዚህ ሄደ ፥ የክብሬም አክሊል ወደቀ፥ ውስጤም ተቃጠለ ፥ ልጄ ከእኔ ሄዷልና ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የነበረን ክብር ከእኛ አለፈ እግዚአብሔርን በማያውቁና ባልታወቁ ሕዝቦች ተወሰደ ። ነቢዩም እንዲህ ብሎ ተናግሯል "ያልፈለጉኝ ሕዝቦች አገኙኝ" ፤ በሌላ ሥፍራም "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ አግዚአብሔር ትዘረጋለች" .... እንደገናም "እነሆ! ከሕግ ውጪ የተወለዱት ፍልስጤም እና ኢትዮጵያ ሕጉ ይሰጣቸዋል ፥ በሚወለደውም ወንድ ልጅ ምክንያት ጽዮንንም (ታቦቱን) እናታችን ይሏታል" ብሎ አዘነ ።

ሰለሞንም ንግሥት ሳባ በልጇና በነጋዴው በታምሪን በኩል የላከችውን መልዕክት አስታውሶ የታቦቱን መክደኛ ጨርቅ ለልጁ ለምኒልክ እዲሰጥ ለዛዶቅ ትዕዛዝ ይሰጣል ። በትዕዛዙም መሠረት ዛዶቅ ለምኒልክ የታቦቱን መሸፈኛ ጨርቅ ይሰጣል ።

ተጓዦቹ መልአኩ ሚካኤል ከፊት እየመራቸውና እየረዳቸው ፥ ከፀሐይም እየከለላቸው የ13 ቀን ጉዞ በአንድ ቀን ተጉዘው በግብጽ ምድር ይደርሳሉ ። በዚያም እረፍት አድርገው ሳሉ አዛሪያስ በምኒልክ ፊት ቀርቦ አንድ ሚስጥር የምናገረው አለኝ ብሎ ታቦቱን በእግዚአብሔር ፈቃድ ይዘውት እንደመጡ ፤ እግዚአብሔርም እንዴት አድርጎ በሕልም እንዳሳየውና ከመቅደሱም ለማውጣት እንዴት እንደረዳቸው ይነግረዋል ። ምኒልክም አያቱ ዳዊት በታቦቱ ፊት በደስታ እንደዘለለ ሁሉ እርሱም በደስታ በታቦቱ ፊት ዘለለ ፤ አብሮ የነበረው ሕዝብም በደስታ ጨፈረ ። ወደ ታቦቱም ቀርቦ ተሳለመ ፥ በላዩም የነቢይ መንፈስ ወረደበት ። ይህ በእንዲህ እንዳለ በኢየሩሳሌም ደግሞ ንግሥት ሳባ በጎበኘችው ጊዜ ያየውን ሕልም ንጉሥ ሰለሞን ለዛዶቅ ያጫውተዋል ። ዛዶቅም በጣም በመደንገጥ የሕልሙ ፍቺ የታቦቱ ከእሥራኤል መወሰድ እንደሆነ ያስረዳዋል ። ወደ ቅድስተ

ቅዱሳኑ ገብቶ በደንብ በተመለከተ ጊዜም አዛሪያ አሠርቶ ለማስመሰል ካስቀመጠው እንጨት በስተቀር ታቦቱ በሥፍራው እንደሌለና እንደተወሰደ ተመልክቶ በድንጋጤ ወድቆ እንደ ሞተ ሰው ሆነ ፡፡

ሰለሞንም በመንገድ ያሉትን ለመያዝ ወታደሮቹን ይልካል ፡፡ ነገር ግን እስከ ግብጽ ድረስ ሄደው ሊደርሱባቸው ስላልቻሉ ተመልሰው ወደ እየሩሳሌም ይመጣሉ ፡፡ እሥራኤላውያን በጣም አዝነው ያለቅሳሉ ፤ በኋላም የእሥራኤል ሽማግሌዎች ለሰለሞን እግዚአብሔር ባይፈቅድ ታቦቱ ሊወሰድ እንደማይችል ይነግሩታል፡፡ ፍልስጤማውያን ከዚህ በፊት ማርከው ወስደውት የነበረ ጊዜ ምን እንደደረሰባቸውና መልሰውም ወደ እሥራኤል እንደላኩት እንዲያስታውስ ያደርጉታል ፡፡ እርሱም ከእንግዲህ ስለታቦቱ መወሰድ እንዳያነሱ ፤ ያልተገረዙት ጎረቤቶቻቸው ሰምተው "ክብራቸው ከእነርሱ ተወሰደ እግዚአብሔርም ጥሏቸዋል ብለው" እንዳይታበዩባቸው ዝም እንዲሉ ያዛቸዋል ፡፡ ሰለሞንም ታቦቱ ከተወሰደ ከ11 ዓመት በኋላ የግብጽ ንጉሥ የፈረኦንን ልጅ ያገባል ፡፡

እርሷ የምታመልከውን ጣኦትም አብሮ ያመልካል ፡፡ በስድሳ ዓመቱ ሰለሞንን በሽታ ይይዘዋል ከዚያም ያርፋል ከአባቱ ከዳዊት ጋራ እንደተቀበረ ክብረ ነገሥት ይዘግባል ፡፡

የኢትዮጵያ ንጉሥ ተብሎ የተቀባው ዳዊት (ምኒልክ) በታላቅ ደስታ ወደ አገሩ ይመለሳል ፡፡ እናቱም ንግሥት ሳባ (ማክዳ) እና ሕዝቡ መምጣታቸውንና ከእነርሱ ጋርም አብሮ ታቦተ ጽዮን መምጣትዋን በሰሙ ጊዜ ታላቅ አቀባበል ያደርጉላቸዋል ፡፡

ንግሥት ሳባም (ማክዳ) የአገሪቱን ሽማግሌዎች ጠርታ ከእንግዲህ በአገሪቱ ላይ ሴት ንግሥትና ከዳዊትና ከሰለሞን ዘር ያልሆነ እንዳይቀመጥ ቃል ኪዳን ታስገባቸዋለች ፡፡ ሕዝቡም ከአስማትና ከጣኦት አምልኮ ተመልሶ ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን ማምለክ ይጀምራሉ ፡፡ አዛሪያና ኤልሚያስ የእሥራኤል የበኩር ልጆች ፤ ካህናት ሆነው ይሾማሉ ፤ ለሕዝቡም ስለ እግዚአብሔር ሕግ እና ስለ ንጹሕና ስለ እርኩስ ምግብ ያስተምራሉ ፡፡

ከዚህ በተረፍ ክብረ ነገሥት ስለታቦቱ የሚናገረው አለ ፡፡ አንደኛው ሃሳብ ታቦቱ የደኅንነት ምልክት እንደሆነ ይናገራል ፡፡ ልክ የኖኅ መርከብ ከውሃ ጥፋት መዳኛ እንደነበር እንደዚሁ ታቦቱ ከእግዚአብሔር ፍርድ መዳኛ እንደሆነ ይዘግባል ፡፡ በመጽሐፉ በስተ መጨረሻም ግሪጎሪ (ጸሐፊው) የሚከተለውን ትንቢት ይጽፋል ፡፡

"እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያና የመንግሥተ ሰማያት ሙሽራ

ስለሆነችው ስለ ታቦተ ጽዮን ያሳየኝንና ያስረዳኝን እጽፋለሁ ::

ኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ እምነቷ እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ ትቀጥላለች ፥ ከሐዋርያት ትምህርትም ፈቀቅ አትልም እስከ ዓለም መጨረሻም እንደዚሁ ይሆናል" :: ይህ ክፍል መጽሐፉ ማለትም ክብረ ነገሥት ከክርስቶስ ልደት በኋላ፥ ክርስትናም ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ እንደዚሁም ኦርቶዶክስ የሚለው ስያሜ በጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ የተጻፈ ለመሆኑ ያመለክታል ::

እንግዲህ ክብረ ነገሥት ስለ ታቦቱ አመጣጥና ስለ ንግሥተ ሳባ ፥ ስለ ንጉሥ ሰለሞንና ስለልጃቸው ስለ ቀዳማዊ ምንሊክ የሚዘግበው ታሪክ ይህንን ይመስላል:: ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከዚህ መጽሐፍ ውጪ ሌላ ይህንን ታሪክ ሊደግፍ የሚችል ምንም ዓይነት ጽሑፍ የለም :: በተለይም ደግሞ ስለ እግዚአብሔር እና ስለእሥራኤላውያን ታሪክ የሚያወራውና በመጀመሪያም ስለታቦቱ የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱስ እንኳ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም አይዘግብም :: በሌሎችም የአይሁድ መጽሐፎች ላይም አልተጠቀሰም :: ይህ ታዲያ የታሪክ ተማራማሪዎችን ግራ ያጋባ ነገር ሆኗል :: ሁሉም የሚጠይቁት በዓለም ዝና ሊገኝለት የማይችለው የአምልኮ ዕቃ እንዴት ከእሥራኤል ታሪክና ከመጽሐፍ ቅዱስ ዝም ብሎ ሊሰወር ይችላል የሚለው ጥያቄ ነው :: ክብረ ነገሥት እንደሚናገረው ከሆነ ድንገትም የእሥራኤል ጎረቤት አገሮች ይህንን ሰምተው ክብራቸውና ግርማቸው ፤ ኃይላቸውም ከእነርሱ ተወስዷልና እንውጋቸው ብለው እንዳይነሱባቸው ሰለሞንና የአገሪቱ ሽማግሌዎች በተማከሩት መሠረት በምስጢር ስለተያዘ ይሆን ? ሌላው ችግር ደግሞ ታቦተ ጽዮንን ከሚጠብቁት ካህን በስተቀር ማንም ሰው ሊያይ ስላልቻለ ፤ ወይም ደግሞ ያየ ሰው ስለሌለ ክብረ ነገሥት የሚዘግበውን ታሪክ ለማረጋገጥ ስላልተቻለ ይሆን ?

ይህ በእንዲህ ሳለ በሌላ በኩል ደግሞ ታቦቱ በኢትዮጵያ ከሌለ በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው የታቦት ሥርዓት ከየት ሊመጣ ቻለ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስም አዳጋች ይሆናል :: ታቦቱ በእሥራኤልም በኢትዮጵያም ከሌለ ታዲያ የት ነው የሚገኘው? በኢትዮጵያ የለም ከተባለ ደግሞ አሁን በአገሪቱ የሚካሄደው ሥርዓት እንዴት ተጀመረ? መልስ የሚያሻቸው ጥያቄዎች ናቸው ::

የክብረ ነገሥትን ታሪክ እንደ መንደርደሪያ ከተመለከትን እንደዚሁ ግራሃም ሀንኮክ የተሰኙት እንግሊዛዊ እአአ በ1992 ዓም The Sign and The Seal በተሰኘው መጽሐፋቸው ታቦቱ የሚገኝበትን

ሥፍራና አመጣጡን ለመመርመር የዘገቡትን ለመመልከት እንሞክራለን ::

ግራሃም ሃንኮክ በጻፉት መጽሐፋቸው የታቦቱን አመጣጥ አስመልክተው እጅግ ሰፋ ያለ ዘገባ አቅርበዋል :: ጠቅለል ባለ መልኩ ሃንኮክ ታቦቱ በኢትዮጵያ ለመኖሩ በፍጹም አይጠራጠሩም:: ለዚህም የሚሆን በቂ ማስረጃ ያቀርባሉ :: ነገር ግን አመጣጡን አስመልክቶ ከክብረ ነገሥት ታሪክ ጋር አይስማሙም ::

ከላይ እንደተመለከትነው ክብረ ነገሥት ታቦቱ በሰለሞን ዘመን በልጁ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ተሰርቆ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ ሲዘግብ ግራሃም ሃንኮክ ግን ይህ ሊሆን አይችልም ባይ ናቸው :: ለዚህም መደገፊያ የሚሆን የተለያዩ ማስረጃዎችን ያቀርባሉ ::

ግራሃም ሀንኮክ በዚሁ መጽሐፋቸው የተለያዩ አገሮችን ማለትም ኢትዮጵያን ፤ በኢትዮጵያም የተለያዩ ሥፍራዎችን እንደ ጣና ሐይቅን ፥ አክሱምን ፥ ጎንደርን ፥ ዝዋይን በመጎብኘት የተለያዩ የቤተ ክርስቲያኖች ካህናቶችን በማነጋገር ፥ ግብጽን እሥራኤልን ፥ ፈረንሳይ እና እንግሊዝንም በማዳረስ ፥ እንደዚሁም በአይሁድ ታሪክና ሃይማኖት ላይ እና በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ብዙ ምርምር ያደረጉ አዋቂዎችን በማነጋገር በሰፊው የተጠናከረ ዘገባ አቅርበዋል::

ይህንን ጥናታቸውን ለማካሄድ ጥረት ባደረጉበት ጊዜ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሌሎችም ታሪኮችን አብሮ አቅረበዋል :: ለምሳሌ በ12ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ከእንግሊዝ አገር Templars የተሰኙ ክርስቲያኖች ሚስጥራዊ በሆነ ሁኔታ ወደ እየሩሳሌም ሄደው በከተማው በሚገኘው የአይሁድ ቤተ መቅደስ ውስጥ ቁፋሮ አካሂደው እንደነበርና በድንገትም ይህን ቁፋሮና ፍለጋ እንዳቋረጡ እንደተገነዘቡ ጽፈዋል :: ፍለጋው በአይሁዶች ዘንድ ታቦቱ ንጉሥ ሰለሞን ገና ከመጀመሪያው ቤተ መቅደሱን ሲያሠራ አዘጋጅቶ በነበረው መደበቂያ ውስጥ ይገኛል የሚለውን እምነት ተከትለው ታቦቱን ለማግኘትና ለመውሰድ ያደረጉት ጥረት እንደነበር ያምናሉ:: ነገር ግን ፍለጋውን በድንገት ያቋረጡበት ምክንያት በዚያን ወቅት ከኢትዮጵያ በስደት ኢየሩሳሌም ይገኝ የነበረው ንጉሥ ላሊበላ ታቦቱ በኢትዮጵያ እንደሚገኝ ስለነገራቸው ሳይሆን አይቀርም ባይ ናቸው::

ከንጉሥ ላሊበላ ጋር የውጭ አገር ዜጎች አብረው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ እንደዚሁም በአሠራሩ ወደር የማይገኝለት ከአንድ ወጥ አለት የተቀረጸውን በላሊበላ የሚገኘውን “የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን” የውጭ አገር ዜጎች (ነጮች)

እንደሠሩት ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ የተሰኙት ፖርቱጋላዊ በጻፉት መጽሐፋቸው ላይ እንደተጠቀሰ ይናገራሉ ። ጽሑፉም " የነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ሥራ በ24 ዓመት ውስጥ እንደተጠናቀቀ እና ይህ እንደተጻፈ እንደዚሁም ሥራው በንጉሥ ሳሊበላ ትዕዛዝ በነጮች እንደተሰራ ነግረውኛል " ይላል ። ከዚህም በተጨማሪ አቡ ሳሊህ የተባሉ ጸሐፊም "የግብጽና የአንዳንድ ጎረቤት አገሮች አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት" በተሰኘው መጽሐፋቸው የእሥራኤል ታቦት በኢትዮጵያ ይገኛል ተብሎ እንደሚታመንና በአንዳንድ በዓላት ላይ ታቦቱን ለማጓጓዝ የሚሸከሙት ነጮች እንደነበሩ ዘግበዋል ።

ሌላው ለመጥቀስ የሚገባው ጉዳይ ግራሃም ሀንኮክ ወደ ዝዋይ ከተማ በመሄድ ያገኙት ግኝት ነው ። በመጀመሪያ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ዝዋይ ከተማ ለመሄድ የተነሳሱበት ምክንያት በአይሁዳዊቷ ዮዲት (ጉዲት) ወረራ ጊዜ ታቦቱን በማሸሽ ከአክሱም ወደ ዝዋይ ተወስዶ ነበር የሚለውን የኢትዮጵያውያንን ታሪክ ለማረጋገጥ ነበር። ቦታው በዝዋይ ሐይቅ የምትገኝ ደብረ ጽዮን የምትባል ደሴት ናት ። ግራሃም ሃንኮክና ሌሎች ከእርሳቸው ጋር የነበሩት በጀልባ ተጉዘው በደሴቷ በደረሱ ጊዜ አንድ የሚያስደንቅ ነገር ገጠማቸው ። ይኸውም የደሴቲቱ ኗሪዎች የሚናገሩት ቋንቋ ትግሪኛ መሆኑ ነበር። ኗሪዎቹ እንዴት ትግሪኛ ሊናገሩ እንደቻሉ በተጠየቁ ጊዜ መልስ ሲሰጡ አባቶቻቸው ከትግራይ እንደሆኑና ከአንድ ሺህ ሠላሳ ዓመት ገደማ በፊት ታቦቱን ከጉዲት አሸሽተው ወድ ዝዋይ አምጥተውት እንደነበረ ገልጸዋል ። እንደዚሁም ታቦቱ ለ72 ዓመታት በዚያ እንደቆየ እና በኋላም ወደ አክሱም እንደተመለሰ ተናግረዋል ።

ከዚህ በተረፈ ግራሃም ሀንኮክ ያነሷቸው እና ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሌሎች ነጥቦች እንደሚከተሉት ናቸው ።

- በመጽሐፍ ቅዱስ (በሰማንያ አሃዱ እትም) በ2ኛ መቃቢያን ምዕራፍ 2 ላይ ነቢዩ ኤርሚያስ ከእግዚአብሔር ባገኘው ትዕዛዝ መሠረት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያወረሰውን አገር ሙሴ ቆሞ የቃኘበት ተራራ ላይ ታቦቱን ይዞት እንደሄደ በዚያም ዋሻ አግኝቶ እንደደበቀው ፤ እግዚአብሔርም ሕዝቡን እንደገና በሚሰበስብበት ጊዜና ምህረቱን እንደገና በሚገልጽበት ጊዜ የተደበቀበት ሥፍራ እንደሚገለጽ ። የብሩክ ራእይ የተሰኘ ጽሑፍ ደግሞ ታቦቱ ባቢሎናውያን እሥራኤልን በወረሩ ጊዜ በቤተ መቅደሱ የሚገኘው

የመሠረት ድንጋይ (በእብራይስጥ "ሸቲያህ" ይባላል) ተከፍቶ እንደዋጠው እንደሚዘግብ ::
ከዚህ በተጨማሪ የአይሁድ ጽሑፎች (ታልሙድ) እንደሚያመለክቱት ቤተ መቅደሱ ለሁለተኛ ጊዜ በተሠራ ጊዜ ከመጀመሪያው ቤተ መቅደስ በአምስት ነገሮች ልዩነት እንደነበረው እንደሚገልጹ ከነዚህም ልዩነቶች መካከል የታቦቱ እና የማስተሰረያው ክዳን አለመገኘት እንደነበር እንደሚያመለክቱ ::

ግራሃም ሃንኮክ ባደረጉት ጥናት መሠረት ታቦቱ ፥ ክብረ ነገሥት እንደሚዘግበው በንጉሥ ሰለሞን ጊዜ በልጁ በምኒልክ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ አይችልም ባይ እንደሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል :: ይህንን እምነታቸውን ከደገፉባቸው ማስረጃዎች መካከል ከዚህ በመቀጠል ሁለቱን እንመለከታለን ::

የመጀመሪያውን ማስረጃ ያቀረቡት በኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ብዙ አስተዋጽኦ ካደረጉት ከዶክተር ሪቻርድ ፓንክረስት ባገኙት ሪፖርት መሠረት ሲሆን ታቦቱ ከምኒሊክ ጋር ከእየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ በአክሱም መቀመጡ ሊሆን የማይችል እንደሆነ ነው :: ምክንያቱም የአክሱም ከተማ በዚያን ገና ያልተቆረቆረች በመሆኗ ነው :: ንጉሥ ሰለሞን በ940 ወይም በ930 ዓመተ ዓለም እንደሞተ ይገመታል :: የአክሱም ከተማ ደግሞ ተቆረቆረች ተብሎ በአርኬዎሎጂ ምርምርና በታሪክ የሚታወቀው ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስተኛው ወይም በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ነው :: በነዚህ ሁለት ጊዚያቶች መካከል ቢያንስ የሰባት መቶ ዓመት ልዩነት አለ ! በዚህ መረጃ መሠረት የክብረ ነገሥት አተራረክ ትክክል አይሁን እንጂ ታቦቱ በዚያ ዘመን ከመጣ በኋላ በሌላ ሥፍራ ተቀምጦ ከጊዜ በኋላ ወደ አክሱም ከተማ ተወስዷል የሚለው ሊያስኬድ ይችላል ::

ሁለተኛውና ጠንካራ መሠረት ያለው የሚመስለው ማስረጃ ግን ግራሃም ሀንኮክ ምርምራቸውን ለማካሄድ በጣና ሐይቅ ፥ ጣና ቂርቆስ በተባለች ገዳም መምህር ፍሰሐ ከተባሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ያገኙት መረጃ ነው:: የታቦቱን አመጣጥ ታሪክ ሲጀምሩ መምህር ፍሰሐ ልክ ክብረ ነገሥት እንደሚዘግበው በሰለሞን ጊዜ በልጁ በምኒልክ አማካኝነት ከእሥራኤል በግብጽ በኩል አባይን ተከትለው ከዚያም የተከዜን ወንዝ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እንዳመጡት ከዘገቡ በኋላ በመቀጠል ግን ታቦቱ

ቀጥታ ወደ አክሱም እንዳልሄደ ነገር ግን ጣና ፣ ቂርቆስ ተብላ በምትጠራው በዚህች ደሴት እንዳስቀመጧት አጫውተዋቸዋል:: ምን ያህል ጊዜ እንደተቀመጠ ሲጠየቁ መምህር ፍስሐ ለስምንት መቶ ዓመት በድንኳን ውስጥ በደሴቷ ላይ እንደቆየና በንጉሥ ኤዛና ዘመነ መንግሥት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ታቦቱ ከጣና ቂርቆስ ወደ አክሱም እንደተወሰደ ይህ ደግሞ በእነርሱ ዘንድ ያለው ታሪክና እምነት እንደሆነም ተናግረዋል ::

ይህ እንደዚህ ከሆነና ታቦቱ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ ከስምንት መቶ ዓመት በፊት ነው መጣ ተብሎ የሚታመነው ከተባለ፣ የመጣበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት ከ400 ዓመት በፊት እንጂ ክብረ ነገሥት እንደሚዘግበው ከ900 ዓመት በፊት አይደለም ማለት ነው ::

መምህር ፍስሐ ከዚህ በተጨማሪ ታቦቱ በደሴቷ ላይ በነበረ ጊዜ እንደ አይሁድ ሕግ መሠረት በታቦቱ ፊት ለሚቀርብ መስዋዕት እና ለደም ስርየት ማሳረጊያ ይጠቀሙበት የነበረበትን ከድንጋይ የተጠረበ የደም ማጠራቀሚያ በደሴቲቱ ላይ እስካሁን እንደሚገኝ አሳይተዋቸዋል ::

ለግራሃም ሃንኮክ ይህ ትልቅ መረጃ ነበር :: በመጀመሪያም የክብረ ነገሥትን ታሪክ እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ይጠራጠሩ ስለነበር (ምንም እንኳ ታቦቱ በኢትዮጵያ መገኘቱን ቢያምኑበትም) የመምህር ፍስሐን መረጃ ሲያገኙ ምርምራቸውን ለመቀጠልና ይህንን ነገር ለማጣራት ጉዟቸውን ወደ ኢየሩሳሌም አደረጉ :: በዚያም ኢትዮጵያዊ አይሁዶችን (ፈላሻዎችን) ለማነጋገር ወስነው ሩፋኤል ሀዳነ የተባሉ ካህን ጋር ይገናኛሉ:: እኚህ ካህን እንግሊዘኛ ስለማይችሉ በልጃቸው በዮሴፍ ሀዳነ በመረዳት ለግራሃም ሀንኮክ እሥራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ በእነርሱ ዘንድ የሚታመነውን ተውፊት አጫውተዋቸዋል ::

ካህን ሩፋኤል ከልጅነታቸው ጀምሮ የሰሙት እና የሚያምኑበትን ታሪክ ሲገልጹ፣ አባቶቻቸው ግብጽ ውስጥ የኖሩ እሥራኤላውያን እንደነበሩ ፣ ግብጽ ውስጥም ለ400 መቶ ዓመት ገደማ እንደኖሩ በዚያም አስዋን በተባለ ሥፍራ ቤተ መቅደስ ሠርተው እንደነበር ገልጸዋል :: ከዚያም የውጭ ወራሪ መጥቶ ግብጽን ባጠቃ ጊዜ በአገሪቱ የሚገኙትን የግብጾችን ማምለኪያ ሥፍራዎች በሙሉ አፍርሶ የእሥራኤላውያንን ቤተ መቅደስ ሳያፈርስ ስለቀረ እሥራኤላውያንን እነዚህ የወራሪ ደጋፊዎች ናቸው ብለው ግብጻውያኖች ቤተ መቅደሱን ስላፈረሱት ከዚያ ተነስተው መሄድ ግድ

ሆነባቸው ። ከዚያም በሱዳን ሜሮኤ (Meroe) በተባለች ከተማ ከተቀመጡ በኋላ በሁለት ተከፍለው በአንድ በኩል በተከዜ ወንዝ አድርገው በሌላ በኩል ደግሞ አባይን ተከትለው በጣና ሐይቅ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ አስረድተዋቸዋል ። ከዚያም በመቀጠል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ካህኑ በጣና ሐይቅ ሦስት ደሴቶች ታላቅነት እንዳለቸው ገልጸው እነዚህም በአንደኛ ደረጃ ጣና ቂርቆስ ፥ በሁለተኛ ደረጃ ደጋ እስጢፋኖስ ቀጥሎም ዘጊ የተባሉት እንደሆኑ ተናግረዋል ።

ግራሃም ሀንኮክ ቃለ ምልልሱን ከማብቃታቸው በፊት የምርምራቸውን ዋነኛ ክፍል ይዞ ያለውን ጉዳይ አስመልክተው "በኢትዮጵያ ያሉት ክርስቲያኖች የቃል ኪዳኑ ታቦት በእኛ ዘንድ በአክሱም ከተማ ነው ፥ የመጣውም በንጉሥ ሰለሞንና በንግሥት ሳባ ልጅ በምኒሊክ አማካኝነት ነው ይላሉ ይህንንስ ይቀበላሉ ወይ?" ብሎ ለጠየቋቸው መልስ ሲሰጡ "አዎ እኔም ሆነኩኝ ሕዝባችን ታቦቱ በእርግጥ በአክሱም እንደሚገኝ እናምናለን ።

እንዲያውም ከተወሰነ ዓመታት በፊት እኔና ሌሎች መንፈሳዊ መሪዎች ከከተማችን ወደ አክሱም ሄደን ታቦቱን ለማየት ሙከራ አድርገን ነበር ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኑን መግባት እንደማይፈቀድልን ተነገረን ፥ እንዲያውም እራሳችን በባህላችን መሠረት አንጽተን እንገባለን ብንልም ሊፈቀድልን አልቻለም እኛም ሳናየው ወደ መጣንበት ተመልሰናል" ብለዋል ።

ግራሃም ሀንኮክ ካህን ሩፋኤልን ካነጋገሩ በኋላ ምርምራቸው ወደ ግብጽ ምድር ወሰዳቸው ። ዓላማቸውም ካህኑ እንደተናገሩት በግብጽ ቤተ መቅደስ ነበረ የሚለውን ለማጣራት ነበር ። ባደረጉትም ፍለጋ በእርግጥም አስዋን በሚባል ከተማ ፥ ኤሌፋንታይን በተባለች ደሴት ላይ እሥራኤላውያን ቤተ መቅደስ ሠርተው እንደነበርና በአምስተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ቤተ መቅደሱ በግብጻውያን እንደፈረሰ በሥፍራው ቁፋሮ ከሚያካሂዱት አርኬዎሎጂስቶች ለመገንዘብ ችለዋል ። ከዚህም በተጨማሪ በሥፍራው እሥራኤላውያኖቹ የመስዋዕት ሥርዓት እንደፈጸሙ መረጃም ለማግኘት ችለዋል ።

ይህ ለግራሃም ሀንኮክ የሚያመለክተው አንድ ነገር ብቻ ነው ። በመጀመሪያ ደረጃ በእሥራኤላውያኖች ዘንድ ቤተ መቅደስ የሚሠራው ለታቦቱ ማደሪያ እንጂ ሌላ ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም ። እንደሚታወቀውም እሥራኤላውያን የነበራቸው አንድ ቤተ መቅደስ ብቻ ነበር ። ሁለተኛ የመስዋዕቱ ሥርዓት የሚከናወነው

ታቦቱ ባለበት ሥፍራ ብቻ ነበር ። በእነዚህ ሁለት አብይ ጉዳዮች ላይ በመመርኮዝ ግራሃም ሀንኮክ ታቦቱ በግብጽ ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን (ከክርስቶስ ልደት በፊት) አንስቶ እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን (ከክርስቶስ ልደት በፊት) እንደነበረ ይገምታሉ ። ይህም ደግሞ መምህር ፍሰሐ ከነገሯቸውና ካህን ሩፋኤል ካጫወቷቸው ተውፊት ጋር የሚስማማ ነው ።

አሁን ደግሞ ግራሃም ሀንኮክ ፥ ምርምራቸው ወደ ሌላ ከተማ ሳይሆን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ወሰዳቸው ። የተመለከቷቸውም የመጽሐፍ ክፍሎች ዜና መዋዕል ካልዕ ምዕራፍ 26 ፥ 33 እና 35 ፤ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 8 እንደዚሁም መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ምዕራፍ 19 እና 21 ናቸው። እነዚህን ሁሉ ክፍሎች ተመልክተው የደረሱበት መደምደሚያ እንደሚከተለው ነው ።

የቃል ኪዳኑ ታቦት ከንጉሥ ሰለሞን በኋላ በመቅደሱ እንደነበር ። ታቦቱ ከቦታው የተነሳው ከንጉሥ ሰለሞን በኋላ ነገር ግን ከንጉሥ ኢዮስያስ በፊት መሆን እንዳለበት ።

አንደኛ በ1ኛ ነገሥት 8፥9 ላይ "እስከ ዛሬም ድረስ በዚያ" ተብሎ መጠቀሱ ታቦቱ በዚያ ሥፍራ እንዳለ ለማሳመን ሆን ተብሎ የተደረገ ሙከራ እንደሆነ። (1ኛ ነገሥት የተጻፈው በ640 - 609 ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደሆነ ይገመታል) ።

በ2ኛ ዜና መዋዕል ከ34፤33 - 35፤3 ድረስ ባለው ምንባብ መሠረት ታቦቱ በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን በሥፍራው እንዳልነበረ ለመረዳት እንደሚቻል ። "... ለተቀደሱት ሌዋውያን እንዲህ አለ (ንጉሥ ኢዮስያስ) - ቅዱሱን ታቦት የእሥራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰለሞን በሠራው ቤት ውስጥ አኑሩት ከዚህም በኋላ በትከሻችሁ ላይ ሸክም አይሆንባችሁም .." ብሎ ንጉሡ ይህንን ሊናገር የቻለበት ምክንያት ታቦቱ በሥፍራው ባይኖር ለመሆኑ በግልጽ ለማየት እንደሚቻል ።

እነዚህን ነጥቦችን መሠረት በማድረግ ንጉሥ ኢዮስያስ የነገሠው በ640 ዓመተ ዓለም በመሆኑ ታቦቱ በሥፍራው ያልነበረው በ955 ዓመተ ዓለም (ከንጉሥ ሰለሞን በኋላ) እና በ640 ዓመተ ዓለም (ከንጉሥ ኢዮስያስ በፊት) መካከል ብቻ ሊሆን እንደሚችል ።

ግራሃም ሀንኮክ በ2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 26፥19 ላይ ባገኙት ምንባብ መሠረት ታቦቱ በ740 ዓመተ ዓለም

በሥፍራው ነበረ ባይ ናቸው ። ይህም የምንባብ ክፍል ያዝያን የተባለ የእሥራኤል ንጉሥ የማይፈቀድለትን በቤተ መቅደስ ውስጥ ገብቶ እጣን ሲያጥን ግንባሩ በለምጽ እንደተመታ የሚገልጸው ክፍል ነው ። በአጠቃላይ ሲታይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች በለምጽ የሚመቱት ታቦቱ በሚገኝበት ሥፍራ እንደነበረ ስለተገነዘቡ ግራሃም ሀንኮክ ንጉሥ ያዚያ ለምጻም በሆነበት ጊዜ ታቦቱ በሥፍራው ነበር ለማለት ደፍሯል ።

ከዚህ በተጨማሪ ታቦቱ በ740 ዓመተ ዓለም ብቻ ሳይሆን በ701 ዓመተ ዓለምም ነበር ። ለዚህ ማስረጃ የሚያቀርቡት በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ምዕራፍ 19÷15 ላይ ነቢዩ ሕዝቅያስ ያቀረቡትን ጸሎት ነው ። በዚህ ጸሎቱ ሕዝቅያስ "በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ" ብሎ በእግዚአብሔር ፊት መጸለዩ በታቦቱ ፊት የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ የሆነውን የስርየት መክደኛውን እየተመለከተ መሆን አለበት ብለው ያመኑበትን ሐሳብ ነው ።

ይህ እንደዚህ ከሆነ ዘንዳ ሕዝቅያስ የሞተው በ687 ዓመተ ዓለም ሲሆን ንጉሥ ኢዮስያስ ደግሞ ወደ ዙፋን የወጣው በ640 ዓመተ ዓለም ነው ። ታቦቱ የጠፋው በነዚህ ሁለት ጊዝያቶች መካከል መሆኑ ነው ። ከ687 እስከ 640 ዓመተ ዓለም መካከል የነገሡት ሁለት ነገሥታት ናቸው ። እነርሱም ንጉሥ ምናሴ (687-642) እና ንጉሥ አሞጽ (642-640) ናቸው ።

ከነዚህ ሁለቱ ነገሥታት መካከል ከፍተኛ ችግር የፈጠረው ንጉሥ ምናሴ ነበር ። በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ምዕራፍ 21÷27 እንደምንመለከተው ምናሴ በጣም አስከፊ ነገር በእግዚአብሔር ፊት አደረገ ። ከሥራውም መካከል ሁሉ አስከፊ የሆነው በቤተ መቅደሱ ውስጥ የተቀረጸ ምስል ማስቀመጡ ነው ። እንደ ግራሃም ሀንኮክ አስተያየት በዚህ ጊዜ መሆን አለበት ይህንን በመቃወም ሌዋውያኑ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከሥፍራው ይዘው የወጡት ። ለዚህም ነው በእሥራኤል ሊቀመጡ ስለማይችሉ ወደ ግብጽ ይዘውት ከመጡ በኋላ በዚያ ማደሪያ ሥፍራ ቤተ መቅደስ ሠርተው (ታቦቱ ወይ በድንኳኑ ማደሪያ ወይ ደግሞ በቤተመቅደሱ ውስጥ ነውና የሚቀመጠው እንደገና ቤተ መቅድስ ለታቦት ማደሪያ ካልሆነ በስተቀር አይሁዶች አልሰሩም) አኑረውታል

ብለው ሊያምኑ የቻሉበት ዋነኛ ምክንያት ::

ይህንን አመለካከት በኢያሩሳሌም ሆነው ከካህን ሩፋኤል ሀዳነ ያገኙትና እደዚሁም በጣና ቂርቆስ ከመምህር ፍሰሐ ያገኙት መረጃ የሚደግፈው ሲሆን ፕሮፌሰር ሜናህም ሃራን የተባሉ እሥራኤላዊ ይህንኑ አመለካከት "ቤተ መቅደሶችና የቤተ መቅደስ አገልግሎት በጥንታዊቷ እሥራኤል" በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩ ለመገንዘብ ይቻላል ::

ለማጠቃለል ያህል ከላይ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ግራሃም ሀንኮክ ታቦቱ በኢትዮጵያ ለመኖሩ ብዙም ጥርጠር የላቸውም :: እንዲያውም ለማየት ፈልገው በጦርነቱ ወቅት እንኳ ወደ አክሱም ተጉዘው በዚያ የታቦቱን ጠባቂ ለማስፈቀድ ጠይቀው ነበር :: የማይቻል ነገር በመሆኑ ታቦቱን ሳያዩት ለመመለስ ተገደዋል:: ነገር ግን የታቦቱን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት አስመልክቶ ከላይ በተመለከትናቸው የምርምር ግኝቶችና ማስረጃዎች ምክንያት የቃል ኪዳኑ ታቦት ክብረ ነገሥት እንደሚዘግበው በቀዳማዊ ምኒሊክ አማካኝነት ሳይሆን ከዚያ በጣም ዘግይቶ በ5ኛው ክፍለ ዘመን (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ወደ ኢትዮጵያ በግብጽ አድርጎ በጣና ቂርቆስ በኩል ወደ አክሱም እንደደረሰ የጥናታቸውን ውጤት አስፍረዋል ::

ይህ ግኝት ብዙ ሊያነጋግርና ሊያከራክር የሚችል ሐሳብ ነው :: ነገር ግን የቃል ኪዳኑ ታቦት ባለቤት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላትን አቋም ፥ እምነት እና አመለካከት እንደዚሁም በታቦቱ ዙሪያ የሚካሄደውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ሥርዓት ለመመልከት ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን፥ ከአይሁድ ሥርዓት ወደ ክርስትና መሸጋገር አስፈላጊ ነው ::

# ታቦት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያን ማለትም ከካቶሊክ እና ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ይቅርና ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት (የግብጽ ፥ የሶሪያ ፥ የራሽያ ፥ የሕንድ ፥ እና የአርመን) ጋር የምትለይበት ዋነኛውና ግምባር ቀደም የሆነው ሥርዓት ሥርዓተ ታቦት ነው ። ከሙሴ ሕግና ከአይሁዳውያን ጋር በተያያዘ የታቦት ሥርዓት በዚህ ዘመን ከኢትዮጵያ በስተቀር በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማይገኝ ሥርዓት ነው ። ይህ እንዴት ሆነ የሚለውን ሐሳብ ወደ ኋላ እንመለከተዋለን ፥ ለጊዜው ግን አጠር አጠር አድርገን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋምና ሥርዓቶች እንመልከት።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መቼ ነው የገባው? ለሚለው ጥያቄ ሁለት አመለካከቶች አሉ ። የመጀመሪያው በአዲስ ኪዳን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 እስከ 40 ባለው ላይ የሰፈረውን በመመርኮዝ ፊሊጶስ ጃንደረባውን ኢትዮጵያዊ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሰከረለትና ካጠመቀው በኋላ ይህ ጃንደረባ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ንግሥት ሕንደኬንና የአገሪቱን ሕዝብ ወደ ክርስትና መልሷል የሚል አመለካከት ባላቸው የሚደገፈው መልስ ሲሆን በዚህ መሠረት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአርባ ዓመተ ምህረት ገደማ እንደሆነና እንዲያውም ኢትዮጵያ ክርስትናን በመቀበል የመጀመሪያዪቱ አገር ናት ተብሎ ይታመናል ። አቶ በላይ ግደይ "የኢትዮጵያ ሥልጣኔ" በተሰኘው መጽሐፋቸው " የቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የአይሁድ ባሕል ተከታዮች ነበሩ ። ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው ከ42 እስከ 52 ዓም ኢትዮጵያንና መሮዌን ትገዛ በነበረችው በንግሥት ህንዳኬ ዘመነ መንግሥት ነው ። ስለ ክርስትና እምነት የሰማችው ኢየሩሳሌም ለስግደት ሄዶ በነበረው እና ሲመለስ ጋዛ ላይ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያ አንዱ በሆነው በፊሊጶስ እጅ በተጠመቀው ጃንደረባዋ አማካኝነት ነው ።

በዚህ ሁኔታ የክርስትና ዘር ተተከለ ከዚያም ቀስ እያለ በአክሱም እምነቱ እየተስፋፋ መጣ ። እንግዲህ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ሁለት ሺህ ዓመት ይሆነዋል" በማለት ዘግበዋል ።ከዚህ የተለየ አመለካከት ያላቸው ደግሞ ክርስትና በሐዋርያት ሥራ በተጠቀሰው

ጃንደረባ አማካኝነት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ለመግባቱ ወይም ለመስፋፋቱ የሚያረጋግጥ ታሪካዊ ማስረጃ የለም ። ነገር ግን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው አባ ሰላማ ተብለው በሚታወቁት የሶሪያ ተወላጅ በሆኑትና የመጀመሪያ ስማቸው ፍሬሚናጦስ በተሰኙት በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው ብለው ያመለክታሉ ።

የአባ ሰላማ አመጣጥ ታሪክ እንደሚከተለው ነው ። አንድ ክርስቲያን ነጋዴ ከጢሮስ ተነስቶ ወደ ሕንድ ጉዞ ያደርግ ነበር ። ከእርሱም ጋር ፍሬሚናጦስና አዲሰስ የሚባሉ ሁለት ወጣቶች አብረውት ነበሩ ። መርከቢቱ በኢትዮጵያ ዳርቻ ላይ ትያዝና ነጋዴው ይገደላል ። ወጣቶቹ ከሞት ተርፈው ወደ አክሱም ወደ ንጉሡ ይወሰዳሉ ። አዲሰስ የጠጅ አሳላፊ ፍሬሚናጦስ ደግሞ ጸሐፊና ጃንደረባ ሆነው ይሾማሉ ። ንጉሡ ኤዛና የተሰኘ ሕጻን ልጅ ትቶ ይሞታል ። ንግሥቲቷም ልጇ ለአቅም አዳም እስከሚደርስ ድረስ እንዳይሄዱና እንዲረዷት በተለይም ፍሬሚናጦስን ትለምንና ምንም እንኳ ንጉሡ ከመሞቱ በፊት ነጻነት ሰጥተዋቸው የነበረ ቢሆንም በዚያው ይቆያሉ።

በዚህ ጊዜ ፍሬሚናጦስ ክርስትናን በማስፋፋት ረገድ ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ንጉሥ ኤዛና በዙፋን ላይ እንደተቀመጡ አዲሰስ ወደ ጢሮስ ሲመለስ ፍሬሚናጦስ ደግሞ ወደ እስክንድሪያ ይጓዛሉ ። በዚያም ለአቡነ አትናሲዮስ በአገሪቱ ክርስትና እንዴት እየተስፋፋ እንደሆነ ገልጸው የተጀመረውን ሥራ ሊቀጥል የሚችል ሰው እንዲላክ ይጠይቃሉ ። አቡነ አትናሲዮስም እርሳቸው እራሳቸውን ቀብተው ወደ ኢትዮጵያ መልሰው ይልኳቸዋል ። ፍሬሚናጦስም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው ሥራቸውን ቀጠሉ በ331 ዓም ንጉሥ ኤዛናን ወደ ክርስትና መልሰው ከዚያም ብዙ እንዳገለገሉና "አባ ሰላማ" ወይም የሰላም አባት የሚል ስያሜ እንዳገኙ ታሪክ ያስረዳል ።

ኦርቶዶክስ ከግሪክ ቃል እንደተወሰደ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይናገራሉ ። ትርጉሙም ቀጥተኛ ወይም እውነተኛ ማለት ነው ። ኦርቶዶክስ በሚል ስያሜ ቤተ ክርስቲያን መጠራት የጀመረችው በተለይም ከኬልቄዶን ጉባዔ ወዲህ ዓለምአቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ባህርይ ላይ ስምምነት ለመድረስ ባለመቻሏ ነው ። አንደኛው ወገን ክርስቶስ ሁለት ባህርይ አለው ሲል (ምዕራብአውያን) ፥ ሌላኛው ወገን የለም ክርስቶስ አንድ ባህርይ (ተዋህዶ) ነው ያለው በማለታቸው ክፍፍል ተፈጠረ ። ባለሁለት ባህርዮቹ ካቶሊክ (ዓለማቀፋዊ) የሚለውን ስያሜ እንደያዙ ሲቀሩ

የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በተለይም የግብጽ ፥ የሶሪያ ፥ የኢትዮጵያ እና የሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ኦርቶዶክስ የሚለውን ስያሜ ይዘው ተለዩ ።

ኢትዮጵያም ከአባ ሰላማ ጊዜ አንስታ እስከ ቅርብ ዓመታት (እስከ አፄ ኃይለሥላሤ ዘመነ መንግሥት) ድረስ ጳጳሶችዋን ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እያስመጣች ክርስትናን አስፋፍታለች ። ይህንኑ አስመልክቶ አባ ኪዳነ ማሪያም ጌታሁን የተባሉ " ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ (ከመሻሻል ጋር)" በተሰኘውና በ1957 ዓም ባሳተሙት መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ ።

"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከግብጻውያን የተወረሰ ነው ። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት ቀዳሚት መሆኗ ቢታወቅ ጳጳስ በመሾምና ጠቅላላውን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በመቀበል የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ትቀድማለች ። ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚባሉት <u>ጥምቀት ክህነት ሜሮንና ቁርባን ተክሊልና ንሰሐ</u> ፤ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ ናቸው ። ከዚህም ሌላ ከነዚህ ጋር ከግብጽ የወረስናቸው ብዙ መንፈሳውያን ልማዶች አሉ እነዚህም ብዙ በዓላትን ማክበር አብዝቶ መጾምና አብዝቶ መጸለይ ናቸው ። እነዚህንም መንፈሳውያን ሕጎች ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሚገባ አክብራና ጠብቃ እስከ ዛሬ ትገለገልባቸዋለች ። ኢትዮጵያ እነዚህን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አጥብቃ በመያዟ እስከዛሬ ተጠቅማባቸዋለች ። ወደፊትም እንደምትጠቀምባቸው ተስፋ አለን" ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብዙውን መንፈሳዊ ሥርዓቶች ከግብጽ ያገኘች ቢሆንም ከግብጽና እንደዚሁም ከሌሎች ምሥራቃዊ ወይም ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን የምትለይበት አለ። ዋነኛ እና ግምባር ቀደም የሆነው ልዩነት የታቦት ሥርዓት ነው። ምንም እንኳ አቡነ ጎርጎሪዮስ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በተሰኘው ጽሑፋቸው "ከኢትዮጵያም ሌላ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ታቦት የተለመደ ሕግ ነው... ለምሳሌ ግብጻውያን ታቦቱን "ሉሕ" ይሉታል ጽላተ ሠሌዳ ማለት ነው" ብለው ቢያመለክቱም የታቦት ሥርዓት ከሙሴ ሕግና ከአይሁዳውያን ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚካሄድ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። የግብጻውያኑን "ሉሕ" በሚመለከት በሚከተሉት ምዕራፎች ይዘረዘራል ።

ታቦት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ማዕከላዊ ሥፍራ ያለው ነው ። ያለ ታቦት ክርስትና እንደዚሁም ያለ ታቦት ቤተ ክርስቲያን ሊኖር እንደማይችል አልፎ ተርፎም ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኛት ታቦቱ በዚያ ሥፍራ መገኘቱ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረተ እምነት ይገልፃል ። (እዚህ ላይ ታቦት እያልን በምንጠቅስበት ጊዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታቦትና ጽላት ያለምንም የቃል/የትርጉም ልዩነት በጥቅም ላይ እንደሚውል ማወቅ አስፈላጊ ነው ። በተለምዶ አነጋገር ታቦት እየተባለ የሚጠቀሰው በጽሑፉ መጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው ሁለቱን ጽላተ ሠሌዳዎች ፥ መናውን ፥ የአሮንን በትር የሚይዘውን በሳጥን መልክ የተሠራውን የአምልኮት ዕቃ ሳይሆን ጽላተ ሠሌዳውን እንደሆነ ከአሁኑ መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል ።)

ብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት የሚያመለክቱ መጽሐፍትን ለመመልከት ብንሞክር በብሉይ ኪዳን ላይ የነበረው የአይሁድ ሥርዓተ ታቦት እንዴት ወደ ክርስትና ይዘት ሊሸጋገር እንደቻለ ሊገልጽ የሚችል ክፍል ለማግኘት አይቻልም ። በእርግጥ የቤተ ክርስቲያንን አቋም ማለትም ለታቦት ስግድትና ክብር እንደሚያስፈልግ ፤ በአንዳንድ ጽሑፎችም አመጣጡ በክብረ ነገሥት ላይ እንደተዘገበው በቀዳማዊ ሚኒሊክ እጅ እንደነበረ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ሥርዓቱን እንደምታከብር የሚገልጹ ክፍሎች ቢኖሩም ፤ ኢትዮጵያ ክርስትና ከተቀበለች በኋላ በተወሰነ ክፍልም ቢሆን ይካሄድ የነበረውን የአይሁድ ሥርዓት በመተው እንዴት ወደ ክርስትና ሥርዓቶች እንደተዘዋወረች፥ ታቦተ ሥርዓቱንም እንዴት ወደ ክርስትና ይዘት ልታመጣው እንደቻለች የሚያመለክት ክፍል ለማግኘት አይቻልም ።

ብርሃኑ ጎበና በ "ዐምደ ሃይማኖት" መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ክርስቲያን አገሮች በተለየ ሁኔታ የብሉይ ኪዳን ሥርዓትና ሕግን ወደ ክርስትና ሕግና ሥርዓት ለውጣ ትጠቀምበታለች ። ይህም ሊሆን የቻለው ከቤተ ይሁዳ ቀጥላ እግዚአብሔርን በመቀበል (በአምልኮተ እግዚአብሔር ውስጥ በመግባት) ከሌሎች ሀገሮች ቀደምትነት ያላት ስለሆነ ነው ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ሕግና ሥርዓት አልፋለች። ከብሉይ ኪዳን ሕግና ሥርዓቶች ብዙዎችን የወሰደች ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ጽላተ ታቦተ ሕግ ነው። አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሰራበት ጊዜ ከጽድ ወይም ከእምነበረድ ተቀርጾ በላዩ የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ስም (ሕቡዕ ስም) አልፋና ኦሜጋ ተጽፎ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሠየማል ።

በቅዳሴም ጊዜ ሕብስቱና ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት ወደ መሆን የሚለውጠው በዚህ በታቦቱ ላይ ነው ፡፡ ስለዚህ ከብሉይ '9ኪዳን ታቦት የሐዲስ ኪዳን ታቦት ለየት ያለ ነው ፡፡ ያ ምሣሌያዊ ሲሆን ይህ ግን አማናዊ ነው ፡፡ የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእሥራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን ነበር በሐዲስ ኪዳን ታቦት ግን የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትቦት ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ እያለ ያመኑትን ሁሉ የሚጠራበት የምሕረት መሰዊያ ነው ፡፡ ክብርና ስግደትም የሚደረግለት ስለዚህ ነው" ፡፡

እንደገናም "መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት" በተሰኘው መጽሐፋቸው ብርሃኑ ጎበና "ታቦት የእግዚአብሔር ቤት ማሕደር ስለሆነ የእግዚአብሔር ማኅደር ለሆነ ታቦት መስገድ ይገባል ፡፡ እግዚአብሔርን በማመን አብነታችን የሆኑ ነቢይ እያሱና ነቢያት ሕገ እግዚአብሔር ለተጻፈበት ስመ እግዚአብሔር ለተቀረጸበት ታቦት ሲሰገዱ ደመ ክርስቶስ ለፈሰሰበት ሥጋው ለተፈተተበት ለታቦት መስገድ እንዴት አይገባም !..... በታቦቱ ላይ የተጻፈው ሕግ ሙሴ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበለው ነው የተጻፈውም በእግዚአብሔር እጅ ነው ፡፡ ይህም ሲሰጠው ለዘላለም ሕግ ሁኗችሁ ይኑር ብሎ ነው ፡፡ ለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕጉ ለዘላለም ጸንቶ እንሚኖር አስረድቷል ፡፡

ጽላቱም ለሙሴ የሰጠው ብቻ ነው እንጂ ሌላ ጽላት ሊኖር አይገባም እንዳይባል የተፈለገው ሕጉ ስለሆነ ሕጉ የተጻፈብት ስሙ የተቀረጸበት ታቦት ሁሉ ማኅደረ እግዚአብሔር ነው ፡፡ ሙሴ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበለው ሕግ ተሽሮ ሕገ ወንጌል ተተክቶበታልና አልፎአል እንዳይባል ጌታ ኦሪትንና ነቢያትን ልሽራቸው አልመጣሁም ፍጹማን ሳደርጋቸው እንጂ ብሎ ሕጉ ዘላለማዊ መሆኑን አስረዳ ፡፡ የቀድሞ ጽላት የእግዚአብሔር ስምንና ሕጉ የተጻፈብት ነበር የዛሬው ታቦት ግን ከኃጢአት በቀር ፍጹም ሰው የሆነ የክርስቶስ አማናዊ ሥጋና ደም የሚሰዋበት ነው" ብለው ጽፈዋል ፡፡

ከሎስ አንጀለስ አሜሪካ ከቅድስት ማሪያም - የኢትዮጵያ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መጋቢት 25 1986 ዓም በታተመ የፕሮግራም መግለጫ ጽሑፍ ላይ ስለ ታቦት እንዲህ የሚል የተመለከተው ማብራሪያ ሰፍሯል ፡፡

"ታቦት ማለት የእግዚአብሔር ማደሪያ የክብሩ ዙፋን ማለት



ካህን በክብረ በዓል ወቅት ጽላት ተሸክሞ



ካህናት በክብረ በዓል ወቅት ጽላት ተሸክመው

ሲሆን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ነው ። ታቦት የተሠራው ከግራር እንጨት ነው ። ታቦቱንና በታቦቱ ዙሪያ የነበሩትን ንዋያተ ቅድሳት ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው በሙሴ አማካኝነት ብልሃትን ጥበብና እውቀትን ማስተዋልን ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠው ባስልኤል የተባለ ሰው ነበር ። ዋና ዓላማው ጽላትን በውስጡ መያዝ ወይም የጽላት ማስቀመጫ ነው ። ጽላት ማለት የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈበት ቅዱስ ሰሌዳ ማለት ነው ። የመጀመሪያውን ሁለት ጽላቶች የተቀረጹት ከድንጋይ ነው ። የቀረጻቸውም እግዚአብሔር ነው ። የጽላት ዋና ዓላማ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ሥም ወይም ለቅዱስ ቃሉ ቅዱስ ሰሌዳ ነው።....... በአጠቃላይ ታቦቱን እግዚአብሔር እራሱ የረቂቅ ኃይሉ ማስተላለፊያ ፥ የአምላክነት ክብሩ መግለጫ አድርጎታል ።

ከዚህም በተረፈ ታቦት በሚወጣበት ጊዜ ሕዝበ እሥራኤል ከታቦቱ 2 ሺህ ክንድ ይርቁ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል ። ብዙ ጊዜ በዓለም ተበትነው የነበሩ ሕዝበ እሥራኤል አሁን ወደ አገራቸው ሲመለሱና ሲሰባሰቡ ታቦቱን ለማግኘት መሬት በመቆፈርና በመፈለግ ላይ ናቸው ። ነገር ግን የተለያዩ የታሪክ ምንጮች እንደሚያስረዱትና እስካሁን ድረስ የታወቁ የታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚናገሩት እኛም እንደምናምነው ከኢየሩሳሌም የመጣ ታቦት ጽዮን በኢትዮጵያ በአክሱም ጽዮን ውስጥ አለ ። ....... ታቦት በአዲስ ኪዳን አልፋ ኦሜጋ የሚለው ቅዱስ ስም እንዲጻፍበት ፥ የጌታ ሥጋና ደም (ቅዱስ ቁርባን) የክብሩ ዙፋን እንዲሆን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተወስኗል (*በየትኛው ቀኖና ወይም በየትኛው ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ግልጽ አልተደረገም*) እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በታቦት ላይ ለፈጸመው ቸርነትና ተአምራትም ሁሉ መታሰቢያ ነው። ...... በአዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት ከኢትዮጵያ ሌላ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትም (Oriental churches) የተለመደ ነው (ግብጽ ፥ሦርያ ፥አርመን ፥ሕንድ) ። የግሪክ የሩሲያ የሩማኒያ ሌሎችም ወደ ክርስትና የተመለሱት ከአረማዊነት ስለሆነ የታቦትን ምስጢር አያውቁትም ። ስለዚህ በታቦት ፈንታ ከመንበር የማይነሣ እንደ ታቦት የሚከበር የጌታ የስቅለቱ ወይም የግንዘቱ ሥዕል ያለበት የነጭ ሐር መጎናጸፊያ አላቸው ። ያለሱ ሥጋ ወደሙ አይፈትቱም ።..... የሮም ካቶሊኮች ደግሞ ሥጋና ደም የሚፈትቱበት "ሜንሳ" ይሉታል ፥ ጠረጴዛ ማለት ነው " ።

ከዚህ ጽሑፍ እንደምንመለከተው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የታቦቱን ሥርዓት ለምን እንደሚከበር ለማስረዳት ያስችል

ዘንድ አመጣጡ ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት እንደሆነና በሙሴ ጊዜ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የተጀመረ ሥርዓት እንደሆነ በማመልከት በተመሳሳይ ሁኔታ አሁንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓቱ መኖሩ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ውጪ ያልሆነ እንደሆነ ለማመልከት ተፈልጎ ነው ። ሆኖም ሥርዓቱ ከአይሁድ ወደ ክርስትና፥ ከቤተ መቅደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደመጣ ግን አያመለክትም ።

በሌላ በኩል ከሥርዓተ ታቦት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሌሎችም በአይሁዶች ዘንድ ይከበሩ እና ይደረጉ የነበሩትን ሥርዓቶች በአብዛኛው ይዛ እንደቀጠለችም መጥቀሱ አስፈላጊ ይሆናል።ይህ አሠራር በተለያየ ጊዜ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሒስ ያስከተለ እንደነበረ ከታሪክ ማህደር ለመረዳት እንችላለን ። ኤድዋርድ ኡለንዶርፍ የተሰኙ ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋ ባህልና ሕዝብ ብዙ መጽሐፍቶችን ያበረከቱ አዋቂ "ኢትዮጵያና መጽሐፍ ቅዱስ" በተሰኘው መጽሐፋቸው ይህን አስመልክተው "የአይሁድ ሥርዓቶች በተለያዩ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ይከበራሉ ። አንዱ የወንድሙን ሚስት ያገባል ፥ ወንዶች ከሚስቶቻቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገቡም፥ ሴቶቹም ልጅ ከወለዱ በኋላ የመንጻታቸው ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ ወደ አምልኮ አይመጡም ፥ መዝሙረ ዳዊትን በዜማ ማንበባቸው ከአይሁዶቹ ጋር ይመሳሰላል ። በመሆኑም በብዙ ነገራቸው ኢትዮጵያውያኖች አይሁድ ይሁኑ ክርስቲያን ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው" በማለት ጽፈዋል ።

እንደገናም ግርማ ዘውዴ "ኢትዮጲስ" በተሰኘው መጽሐፋቸው አቡነ ሰላማ ክርስትናን በኢትዮጲያ በመሠረቱበት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን አመራር የአይሁድ ወገኖችን እንዲመረጡ ካስረዱ በኋላ "ነገር ግን በአይሁዳዊ እምነት የነበሩ ሰዎች ወደ ክርስትና እምነት ቢገቡም አንዳንድ ሥርዓትና ልማድ ለመተው እንደማይቻላቸው ቅዱስ ጳውሎስን ሲቃወሙ የነበሩትን የአይሁድ ክርስቲያኖች አስታውሶ ማመዛዘን ነው ። በዚህም ሆነ በሌላ ምክኒያት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማይገኙ አንዳንድ ባህሎች በኢትዮጲያ ሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ ነባር ልማድ ሆነው መቅረታቸው የመጀመሪያዎቹ ካህናትም ሆኑ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ጳጳሳት ችላ በማለታቸውና ለማስተካከል ባለመጣራቸው እንደሆነ ይገመታል ። እነርሱም እያወቀ ሲሄድ ጎጂውን ባህል ራሱ ይተዋል በሚል ዘይቤ ችላ ስላሉት ሥር እየሰደደ ሄደ" ብለዋል። ነባር ልማድ ሆነው የቆዩትም ፤

ሀ) የቤተ መቅደስ አራታዊ አሠራር
ለ) የቤተ መቅደስ መጋረጃ
ሐ) የካህናት ጥምጥም
መ) ግርዘት
ሠ) ዋዕለ ንጽሕ (የመንጻት ወራት)
ረ) ሕጽበት (መታጠብ)
ሰ) ርቅየት (መርጨት)
ሸ) ደመትክቶ (የሴት የወር አበባ)
ቀ) ህርመተ መባልዕት (መብልን እርኩስና ቅዱስ ብሎ መለየት)

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የአሪት ልማዶች እንደነባር ባህል ሆነው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰርገው ሲገቡ አቡነ ሰላማም ሆነ በኋላ የመጡት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ሁኔታውን እንደቀላል ነገር በመቁጠር ጭቅጭቅም እንዳይፈጥር በማሰብ ትተውታል ። ምናልባትም በገላቲያ 2፥ 11-12 እንደተጠቀሰው የጴጥሮስንና የያዕቅብን ፈሊጥ ተከትሎ ወደ ፊት ቅዱሳት መጽሐፍት እያጠኑና እያወቁ ሲሄዱ ይተዋሉ በማለት ይሆናል የሚል ግምትም አሳድሮአል ። ይሁን እንጂ በየዘመኑ የተነሱት አንዳንድ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ማብራሪያ በመስጠት ልማዳዊ ሆኖ የኖረው የአይሁድ ባህል እንዲቀር ማረማቸው ቢታወቅም በሕዝቡ ዘንድ ግን ነባርና የፀና ልማድ ሆኖ ስለቆየ ሊወገድ አልቻለም" በማለት ግርማ ዘውዴ ዘግበዋል ።

ግርማ ዘውዴ በጠቀሷቸው ላይ የሰንበትን ጉዳይ ጨምሮ በነዚህ ሥርዓቶች ላይ ብዙ ውዝግብ ተነስቶ እንደነበረ የታሪክ ተማራማሪዎች ይዘግባሉ ። የአይሁድ ሥርዓትን በተመለከተ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አቋም ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳን አገር የነበረችው ኢትዮጵያ በክርስትና ጊዜም ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን ጠቃሚ ነገሮች በክርስትና መንፈስ እየተረጎመች ትጠቀምባቸዋለች የሚለው ነው ።

ከታሪክ ማህደር የምንመለከተው ግን የአይሁድ በዓልና ሥርዓት መከበር አለበት እና የለበትም በሚሉ ሁለት ክፍሎች በተደጋጋሚ ግጭትና ክርክር ይነሳ እንደነበረ ነው ። በዚህም ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ አርቶደክስ ቤተ ክርስቲያን አቋም ከመጀመሪያው ምን እንደነበረ ለመገመት አወዛጋቢ መስሎ ይታያል ። ለምሳሌ ያህል የሰንበትን (ቅዳሜ ወይስ እሁድ) ጥያቄ አስመልክቶ ኤዎስጣጤዎስ የተሰኙ መነኩሴ ከአገሪቱ ተሰድደው እንደነበረ ታደሰ ታምራት መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በተሰኘው መጽሐፋቸው ይዘግባሉ ።

እኚሁ መነኩሴ ቀዳሚት ሰንበትን በማክበራቸው ስደት ደርሶባቸው እንደነበርና ግብጽ እያሉ በፓትርያርኩ ዘንድ ቀርበው የተሰነዘረባቸውን ክስ እንዳመኑና እርቅ እንዲፈጥሩ በተጠየቁ ጊዜም ተናደው ለፓትርያርኩ "ወደ አገርዎት የመጣሁት ለእግዚአብሔር ቃል ለመሞት ቆርጬ ነው ። ምክንያቱም በዚህ ዓለም ምንም እረፍት አላገኘሁም ። ኢትዮጵያ እያለሁ ቀዳሚት ሰንበትንና ሌሎችንም የእረፍት ቀናት እንደኛ አፍርስ ቢሉኝ አሻፈረኝ አልኩኝ። እዚህ ደግሞ የእረፍት ቀናትን ሳታከብሩ በጸሎት አንድ እንሁን ትሉኛላችሁ" ብለው እንደመለሱ ታደሰ ታምራት በመጽሐፋቸው ዘግበዋል ።

የአይሁድ ሥርዓትን መጠበቅና አለመጠበቅ ቀዳሚት ሰንበትን በተመለከተ ብቻ አይደለም ግዝረትን ፥ ንጹሕና እርኩስ መብልን በመጠበቅም አኳያ ነው ። በነዚህም ጉዳዮች ላይ በየጊዜው ጥያቄ እየተነሳ መልስ ሲሰጥበት ቆይቷል ። መልስ ከሰጡት መካከል ንጉሥ ገላውዴዎስን መጥቀስ ይቻላል።

> "የቀድሞውን የሰንበተን ቀን (ቅዳሜን) ስለማክበር ደሙ በእኛ እና በልጆቻችን ላይ ይሁን ብለው ክርስቶስን እንደሰቀሉት አይሁዳውያን አናከብረውም ። ምክንያቱም አይሁዶች ውሃም አይጠጡም እሳትም አያነዱም ምግብም አያበስሉም ዳቦም አይጋግሩም ከቤት ወደ ቤትም አይንቀሳቀሱም ። እኛ ግን አባቶቻችን በዲዳስቃሊያ እንዳሰፈሩት ቁርባንንና የፍቅር ገበታን በማዘጋጀት እናከብረዋለን ። እንደሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን (እንደ እሁድ) አናከብረውም ። ይህ (እሁድ) አዲስ ቀን ነው ይህንንም በተመለከተ ዳዊት ጌታ የሠራት ቀን ይህች ናት ... ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ቀን ከሞት ተነሣ በዚህችም ቀን መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያት ላይ ወረደባቸው በዚህም ዕለት ከቅድስት ድንግል ማሪያም ተጸነሰ ለጻድቃን ዋጋቸውን ሊሰጥ በኃጢአተኞች ላይም እንደ ሥራቸው ሊፈርድ ይመለሳል ።
>
> አሁንም የግዝረቱን ጥያቄ በተመለከተ እንደ አይሁዶች አንገረዝም ምክንያቱም የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለን ። "መገረዝም አለመገረዝም አይጠቅምም የሚጠቅምስ አዲስ ፍጥረት መሆን ነው " ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው ። .... በእኛ ዘንድ የሚፈጸመው መገረዝ እንደ አገራችን ባህል ነው ልክ ኢትዮጵያውያኖችና የኑቢያ ተወላጆች

ፊታቸውን እንደሚነቀሱ ፥ ሕንዶችም ጆሮአቸውን እንደሚበሱ ነው ። የምናደርገውም የሙሴን ሕግ በማክበር ሳይሆን እንደሕዝቡ ባሕል ነው ። በመጨረሻም የአሳማ ሥጋ ስለመብላት አይሁዶች በሙሴ ሕግ እንደሚከለክሉት የአሳማ ሥጋ ከመብላት አንከለክልም ። የሚበሉትን አንጠላቸውም እርኩስም አድርገን አንቆጥራቸውም ፥ የማይበሉትን እንዲበሉ አናስገድዳቸውም። አባታችን ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሲጽፍላቸው " በእምነት የደከመውን ተቀበሉት በአሳቡም ላይ አትፍረዱ። ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደተፈቀደለት የሚያምን አለ ደካማው ግን አትክልት ትበላል ። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና" ። ስለዚህ ምግብ ሁሉ ንጹሕ ነው።

እነዚህ መልሶች የተሰጡት በየጊዜው ከየአቅጣጨው ይሰነዘሩ ለነበሩ ክሶች ነው ። ክሱ በተለየ ይሰነዘር የነበረው ከእሴክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ነበር። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአይሁድን ባህልን አሁንም ትከተላለች ይህ ደግሞ ክርስቲያናዊ ይዘት የለውም የሚል ሲሆን መልሱ ደግሞ ሥርዓቶቹን ብንከተላቸውም የአይሁድን ባህል በመከተል ሳይሆን ሲደረጉ ስለቆዩና ከአገሪቱ ባህል ጋር ስለተዋሐዱ እንጂ ሃይማኖታዊ ይዘት የላቸውም የሚል ይመስላል ።

ጉዳዩ የበለጠ አወዛጋቢ ሆኖ የሚገኘው በተለይም በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች (ካህናት) ዘንድ የሥርዓቶቹ መከበር እንዲጠብቁ ትምሕርት መሰጠቱ ነው ። ሌላው አወዛጋቢ ጉዳይ ምንም እንኳ (በተለየ) ቀዳሚት ሰንበተን ከእሁድ ጋር ደምሮ ማክበር እንደሚገባ በንጉሥ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ትዕዛዝ የወጣ ቢሆንም ፤ እስካሁን ድረስ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ፍትሐ ነገሥት ላይ ቀዳሚት ሰንበትን እና ርኩስና ንጹሕ ምግብን አስመልክቶ ተጽፎ የምናገኘው ከሚደረገው ፥ ከሚነገረውና ፥ ከሚሰራበት ጋራ በፍጹም የማይገናኝ መሆኑ ነው ። ፍትሐ ነገሥት ምዕራፍ/አንቀጽ 19 "ክርስቲያን እንደ አይሁድ በዕለተ ቀዳሚት ተግባርን ማጉደል አይገባቸውም በዚያች ዕለት እንደ ክርስቲያን ይሥሩ እንጂ ። ከሕዝቡ ወገን የአይሁድ ሥራ ሲሠሩ ቢገኙ እነርሱ ከክርስቶስ ፊት የተለዩ ይሆናሉ ። ..... እንደ አይሁድ ቀዳሚትን አትጠናቀቁ ። ..... በእሁድና በተከበሩት በዓላት ቀን ስግደት አይገባም እነዚህ የደስታ ቀኖች ናቸውና ። ስለዚህ በእሁድና በበዓላት ቀን ሥራ መፍታት ይገባል ። ይህ ያልተወገዘበት አንቀጽ

ነው" ይላል ። ርኩስና ንጹሕ ምግብን በተመለከተ ደግሞ አንቀጽ 23 ላይ "ሐዋርያት በግብረ ሐዋርያትና በሲኖዶሳቸው በግድ ከምትተውት ከዚህ በቀር የበለጠ ከባድ ሸክም በላያችሁ እንዳናኖር እነሆ መንፈስ ቅዱስ ፈቅዷል እኛም ደግሞ ፈቀድን ብለው ከከለከሉት በቀር በክርስቶስ ሕግ የሚከለከል መብል የለም። ይኸውም ደምን ፥ ታንቆ የሞተውን ፥ ለጣዖት የተሠዋውን ፥ አውሬ የነከሰውን ከመብላት ትከለከሉ ዘንድ ነው" ይላል ።

ይህ ሁሉ ሲጠቃለል በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አቋም መሠረት ከአይሁድ ባህል ክርስቲያናዊ ይዘት አየተሰጣቸው የተመለሱት ሥርዓቶች በሙሉ አግባብነት አላቸው የሚለውን አመለካከት ለመቀበል አስቸጋሪ ሆኖ እናገኘዋለን ። በአንድ በኩል በቤተ ክርስቲያን ካህናቶች ሥርዓቱ መጠበቅ አለበት የሚል አቋም አለ ። እንዲያውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሙሴን ሕግ ልሽር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ ብሏልና በሙሴ ሕግ የተጻፉትን ሕግጋት መፈጸም አለብን የሚል ጠንካራ አቋም ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቀደም ሲል እንደተናገሩትም ሆነ በመጽሐፍትም ላይ እንዳሰፈሩት ፤ ከላይ እንደተመለከትነው ደግሞ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ገላውድዮስ በሰጡት የእምነት መግለጫ እንደምናየውና በቅርቡም አባ ጎርጎሪዮስ የቀድሞው የአ አ ጳጳስ ካሳተሙት መጽሐፋቸው የአይሁድ ባህል ቀድሞ ይከበር ስለነበር በዚያው የቀጠለ እንደሆነ እንረዳለን ። የአፄ ገላውድዮስ የእምነት መግለጫ አገላለጽ እንዲያውም አይሁዶች ያደርጉት የነበረው ወይም እያደረጉ ያለው ሥርዓት ትክክል አይደለም የሚል መልዕክት የሚያስተጋባ ይመስላል ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደግሞ በሌላ ወገን ቀዳሚት ሰንበት መከበር የለበትም ፤ የምግብ ክልክል የለውም እያለ ማስተማሩ ትኩረት ሰጥቶ ለተመለከተው ውዝግብ እንደሚፈጥር ለመረዳት አያዳግትም ። የትኛው ነው ትክክል ፥ የትኛውን መከተል አለብን ቢባል ግልጽ የሆነ መልስ አይገኝለትም።

ክርስትና በመጀመሪያ ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ወደ የአቅጣጨው በተስፋፋበት ጊዜ በሕግና በሥርዓት አጠባበቅ ላይ ተመሳሳይ ውዝግብ ተነስቶ እንደነበር ቀደም ብለን ተመልክተናል ። ከአይሁድነት የተመለሱት ክርስቲያኖች የለም ሥርዓቶቹ መጠበቅ አለባቸው የሚል አቋም ይዘው ሲነሱ አረማውያን የነበሩት ደግሞ ግዴታ የለብንም ብለው ክርክር ገጠሙ። ይህንንም ሁኔታ ግልጽ ለማድረግና እውነተኛውንና ትክክለኛውን የክርስትና ትምሕርት ለማስተማርና

ለማስተላለፍ ሲል ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙውን የትምሕርቱን ክፍል በዚህ ጉዳይ ላይ ያሳለፈው ::

የመጀመሪያዎቹ የክርስቲያን አባቶች ክርስትና አዲስ ሃይማኖት እንዳልሆነ ፥ ይልቅስ እግዚአብሔር ከፍጥረት ጀምሮ በዘላለማዊ ዕቅዱ ውስጥ ያዘጋጀውና የደነገገው ፥ በነቢያት የተተነበየ፥ በነገሥታት የተነገረለት ፥ በእሥራኤላውያን ሲጠበቅ የነበረ ክስተት እንደሆነ በማስረዳት እንዳስተማሩ ሁሉ ! የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስትና ይዘት የሚደረገው የታቦት ሥርዓተ አምልኮ ከብሉይ ኪዳን የመጣና ከክርስትና ጋር ተስማምቶ ተመቻችቶ የተደነገገ ሥርዓት ነው የሚል አቋም እንዳላት ለማየት ችለናል ::

ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ ሥርዓቱ በኢትዮጵያ ብቻ መገኘቱ ደግሞ ይህንን አቋም ሊያናጋ የሚችል ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን :: በኋላ እንደምንመለከተውም ሥርዓቱ ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋር እጅግ በጣም የተለየ መሆኑ ተጨማሪ ችግር ይፈጥራል ::

ሥርዓተ ታቦት ከብሉይ ኪዳን ወደ ክርስትና እና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊተላለፍ/ሊሸጋገር እንደቻለ ፥ ይህም መቼ እንደሆነ የሚገልጽ አንድም የቤተ ክርስቲያን መዝገብ ወይም ታሪካዊ ጽሑፍ ለማግኘት አይቻልም :: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊነቱ ግን የግድ ነው ::

አንድ የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "መሪ ጌታ" የሆኑ አገልጋይ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል :: "ታቦቱ የቤተ ክርስቲያኒቷ መካከለኛና ዓቢይ የአምልኮ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ነው:: ያለ ታቦቱ ቤተ ክርስቲያን ሊኖር አይችልም :: ቤተ ክርስቲያኒቱንም ቤተ ክርስቲያን የሚያስብላት የታቦቱ በዚያ ሥፍራ መገኘት ነው :: አስፈላጊነቱም ሥጋ ወደ ደሙ የሚፈተተው በዚሁ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ስለሆነ ነው" :: እኚሁ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሲያስታውቁ "ያለ ታቦቱ አይቀደስም ...." እንደገናም "አስፈላጊነቱ ግን የግድ ነው" ብለዋል ::

"አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሰራበት ጊዜ" ይላሉ ደግሞ የቀድሞው አቡነ ጎርጎሪዮስ "ከዕፅ ወይም ከእምነበረድ ተቀርጸ የእግዚአብሔር ሚስጥራዊ ስም (ኅቡዕ ስም) አልፋና አሜጋ (የመጀመሪያውና የመጨረሻው ማለት ነው) ይጻፍበታል :: ይህ ቃል ከተጻፈበት በኋላ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሰየማል :: በቅዳሴም ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ

መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት ወደ መሆን የሚለውጠው ከዚህ በታቦቱ ላይ ነው ::

በዚህ ገለጻ መሠረት የታቦቱ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መገኘት በብሉይ ኪዳን መሠረት የእግዚአብሔር ክብር መገኛ ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳን መሠረት ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ባዘዘው መሠረት ሥጋና ደሙን (የቁርባን ሥረዓት) ለማሳረግ የምንጠቀምበት ነው ማለት ነው ::

# ታቦት በቤተ መቅደስና በቤተ ክርስቲያን ፤ ተመሳሳይነቱና ልዩነቱ

ታቦት ከጅምሩ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንዴት ሊሠራ እንደቻለ ፤ ቅርጹ ምን እንደሚመስል ፤ በዙሪያው የነበረው አምልኮና ሥርዓት ምን እንደሚመስል ፤ በሚገርም ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሊሰወር እንደቻለ ፤ እንደ ክብረ ነገሥት እና እንደ ግራሃም ሀንኮክ አባባል (በተለያየ መንገድ ቢሆንም) ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ሊመጣ እንደቻለ ፤ ከዚያም ዛሬ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን (ብቻ) በምን ጥቅም ላይ እንደሚውል ተመልክተናል:: እንደገናም ባጭሩ ታቦትና ጽላት ፤ ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ቢሆኑም በማፈራረቅ ልዩነት ሳናደርግ በዘልማድ እንደምንጠቀምባቸውም ተመልክተናል ::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአርቶደክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጨማሪ የአይሁድ ባህሎች ዛሬም በመከበርና ሥርዓታቸው በመፈጸም ላይ እንደሆነም ዳስሰናል ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታቦቱ ከአይሁድ ባህልና ሥርዓት ወደ ክርስትና ይዘት በተዘዋወረበት ጊዜ በርከት ያሉ ልዩነቶችን እንደሚያሳይ ቀጥለን እንመለከታለን :: ከዚያ በፊት አልፎ አልፎም በምእመን ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም ዘንድ የተሰሳተ አመለካከት እንዳለ ለመገንዘብ ያስችለን ዘንድ አባ ኪዳነ ማሪያም ጌታሁን ስለ ታቦት ሲጽፉ ያሉትን መጥቀስ ጥሩ ይሆናል ::

“.... እግዚአብሔር ለሙሴ <u>ሁለቱን ታቦቶች</u> እንደሰጠው ተገንዝበናል ከነዚህ ከ2ቱ አንዷ ወደ ኢትዮጵያ መጥታ በአክሱም ገዳም ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች የመጣችውም በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው :: ታቦተ ጽዮን ከልደተ ክርስቶስ በፊት በኢትዮጵያ የኖረችው 982 ዓመት ነው ” በማለት አስፍረዋል :: እንደገናም ስለ ታቦቱ አስፈላጊነት እንዲያብራሩ የተጠየቁ አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በሰጡት መልስ “... ቤተ እሥራኤል ሀገራቸው ከገቡ በኋላ ግን መጠባበቂያ ሠርተው እንደነበር ክብረ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ያስረዳል :: እንዲያውም ከንጉሥ ምኒልክ ቀዳማዊ ጋር የብሉይ ካህናት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የሚያመልኩበት ታቦት እንዲሰጣቸው ስለሞንን ቢጠይቁት እንዲወስዱ የፈቀደላቸው ተመሳሳዩንና በኋላ የተሠራውን ሲሆን እነርሱ ግን ገብተው

ከመቅደሳቸው ዋናውን አምጥተዋል" ብለዋል ። በመጀመሪያው የአባ ኪዳነ ማሪያም አገላለጽ ላይ ታቦት ተብሎ የተጠቀሰው (እንደእርሳቸው አመለካከት) ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውንና አሥርቱ ትዕዛዛት የሠፈሩበትን ሁለትን ጽላቶች ሲሆን ፤ አንደኛው ጽላት (ምናልባትም አምስቱ ትዕዛዘት የሠፈረበት!) በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ የሚያመለክት ነው ። በዚህ አገላለጽ መሠረት ታቦቱ ከጽላቶቹ ጋር ተመሳስሏል ። በሁለተኛው አገላለጽ መሠረት ግን በአፈ ታሪክ ካልሆነ በስተቀረ በክብረ ነገሥት ላይ ሌላ ታቦት ለመሠራቱ የሚያመለክት ሥፍራ የለም ፤ ቀደም ብለን የክብረ ነገሥትን ንባብ በተመለከትንበት ጊዜም እንደተረዳነው የብሉይ ካህናት በታቦቱ ምትክ የእንጨት ርብራብ ትተው እንደሄዱና ታቦቱን ለመስረቅ የተነሳሱበት ምክንያት ብቻችንን አንሄድም ፥ የምናገለግለውን ታቦት ይዘን እንሄዳለን በሚል እንደሆነ ተረድተናል ።

አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያለው ታቦት ማለትም በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኘው ከአይሁድ ሥርዓተ ታቦት ጋር ብዙ ልዩነት አለው ።

1ኛ) በብሉይ ኪዳን ጊዜ ታቦቱ አንድ ብቻ ነበር ። ለእርሱም ማደሪያ የተሠራው አንድ ቤተ መቅደስ ብቻ ነበር ። ሌላው እንኳ ቢቀር ታቦቱ በተሰረቀ ጊዜ እና አይሁዶች በተለያየ ጊዜ በምርኮ በየአገሩ በተበታተኑበት ጊዜ በአቅራቢያቸው እንዲኖራቸው ሌላ ታቦት እንዳልሠሩ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከታሪክ ማህደር ለመረዳት አንችላለን ። ይህ ቢሆንማ ኖሮ ዛሬ በየከተማው ባላቸው ቤተ ምኩራብ ታቦት ይኖራቸው ነበር ፤ ወይም በየከተማው ቤተ መቅደስ ይኖራቸው ነበር ፤ ታቦቱ እንደ ክብረ ነገሥት ዘገባ ከቤተ መቅደሱ ተሰርቆ በተወሰደ ጊዜ ሌላ በትዕዛዙ መሠረተ ሠርተው ሊተኩ ይችሉ ነበር ። ነገር ግን አልሆነም ። ተሰደው በነበር ጊዜም ሌላ ታቦትና ለማደሪያው ቤተ መቅደስ ባለመስራታቸው እሥራኤላውያን በየጊዜው ወደ ኢየሩሳሌም እየተጓዙ በዓላቸውን ማክበረ ነበረባቸው።

በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ዘንድ በእርግጥ እውነተኛው (ኦሪጂናሉ) ታቦት በአክሱም ከተማ ይገኛል ተብሎ ቢታመንም በየከተማው ፥ በየቤተ ክርስቲያኑና በየአገሩ ኮፒ ታቦት አለ ። ይህ በመጀመሪያ ከነበረው አሠራር የተለየ እንደሆነ እንረዳለን ። ለዚህም መልስ ለመሻት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን አነጋግሬ ነበር ። አንዳንዶቹ እሥራኤላውያን ተመሳሳይ ታቦት ሠርተው እንደነበር ገልጸውልኛል ። "ቤተ እሥራኤል ሀገራቸው እስኪገቡ ድረስ ሌላ

አላስፈለጋቸውም ነበር ። ሀገራቸው ከገቡ በኋላ ግን መጠባበቂያ ሠርተው እንደነበረ ክብረ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ያስረዳል ። እንዲያውም ከንጉሥ ምኒሊክ ቀዳማዊ ጋር የብሉይ ካህናት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የሚያመልኩብት ታቦት እንዲሰጣቸው ሰለሞንን ቢጠይቁት እንዲወስዱ የፈቀደላቸው ተመሳሳዩንና በኋላ የተሠራውን ሲሆን እነርሱ ግን ገብተው ከመቅደሳቸው ዋናዋን አምጥተዋታል ። በሃገራችን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ብዙ ጽላት ቢኖር አንድ ዓይነት የጌታ ቃል ተጽፎበት በአንድ ዓይነት ሥርዓት ተቀድሶ አንድ ዓይነት ምስጋና ይቀርብበታልና መሥዋዕተ እግዚአብሔርም በየቦታው ይፈተትበታልና .... ያለ እርሱም አይቀደሰም" በማለት ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ አስታውቀዋል ።

2ኛ) ሌላው ዋነኛ ልዩነት በጽላቱ ላይ የተጻፈው ነው ። በመጽሐፉ መጀመሪያ ክፍል ስለ ታቦቱ ቅርጽና የሥራ ትዕዛዝ በተመለከትን ጊዜ ሙሴ ታቦቱን ሠርቶ ሲያበቃ እግዚአብሔር በሲና ተራራ በጣቶቹ አሥርቱን ቃላት የጻፈባቸውን ሁለት ጽላቶች ሰጥቶት በታቦቱ ውስጥ እንዲያኖራቸው እንዳዘዘው እናስታውሳለን ። በአሁኑ ጊዜ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሚገኙት ጽላቶች ግን የሚጻፈው አሥርቱ ቃላት ሳይሆን ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አልፋ እና ኦሜጋ የሚለው የእግዚአብሔር ስም ነው ።
ብርሃኑ ጎበና እንደገለጹት "አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሠራበት ጊዜ ከጽድ ወይም ከእምነበረድ ተቀርጾ <u>በላዩ የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ስም( ሕቡዕ ስም) አልፋና ኦሜጋ ተጽፎ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሠየማል</u>"። ይህ ልዩነት ለምን እንደሆነ እንዴትም እንደመጣ ግልጽ የሆነ ነገር የለም ።

3ኛ) ከዚህ ሌላ ያለው ልዩነት የጽላቶቹ ዓይነቶች ነው ። ከአቡነ ጎርጎሪዮስ እና ከብርሃኑ ጎበና መጽሐፎች እንደተረዳነው ጽላቶቹ ከጽድ ወይም ከእምነበረድ ሊሆኑ ይችላሉ ። ነገር በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው ጽላቶች ከድንጋይ የሆኑ ጽላቶች ነበሩ እንጂ ከጽድ ወይም ከእንጨት አልነበሩም ። ድንጋዩም ከእምነ በረድ ለመሆኑ እርግጠኞች አንሆንም ።

"እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው " (ኦሪት ዘጸአት ም 31 ፥ 18) ። "ሙሴም እንደፊተኞቹ አድርጎ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠረበ በነጋውም ማልዶ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደ ሲና ተራራ ወጣ

ሁለቱንም የድንጋይ ጽላቶች በእጁ ወሰደ ...” (ዘጸአት 34 ፥ 4) ።

4ኛ) ሌላው የታቦቱ መሰየም አንድ ልዩነት ነው ። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ታቦቱ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ፥ የምሥክሩ ታቦት፥ ቅዱሱ ታቦት እና የመቅደሱ ታቦት እየተባለ ይጠራ ነበር ። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ታቦቱ በተለያዩ ቅዱሳን፥ በመላዕክት፥ በድንግል ማሪያም ሰም እንደሚጠሩ ወይም እንደሚሰየሙ እናውቃለን ። ከዚህ በተጨማሪም በክብረ ነገሥት በተዘገበው ታሪክ ላይ ታቦቱ በአንስታይ (ማለትም አንቺ ወይም እርሷ) እንደሚጠራ እና ጽዮን እንድሚባልም ታሪኩን በዳሰስንበት ጊዜ ለመመልከት ችለናል ። ይህ ከአይሁድ ሥርዓት የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ለዚህ ማብራሪያ ለማግኘት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ ሰው ሲገልጹ “በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማሪያም በጻድቃን ወዘተ..... ለምን ተሰየመ ቢባል በአማልጅነታቸው ለመጠቀም ሲባል በስማቸው ይሰየማል እንጂ በጽላቱም የሚጻፈው ያው አንድ ዓይነት ቃል ነው ሥርዓቱም በዚያው የሚፈጸም ነው” በማለት ገልጸዋል ። ይህንን የመሰየም ነገር በተመለከተ ሌሎች ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ምኒሊክ እጅ የመጣው ታቦት የሚካኤል ታቦት ነው ተብሎ እንደሚታመን ገልጸዋል ። ነገር ግን ይህ አፈ ታሪክ ድንገትም በክብረ ነገሥት ላይ ታቦቱ ከእሥራኤል ተሰርቆ ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ በተጀመረበት ጊዜ ንጉሡንና የተከተሉትን ሁሉ ይመራ የነበረው መልአኩ ሚካኤል ነው ብሎ ከተዘግበው ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ።

5ኛ) ቀጥሎ ከአይሁድ ባህል ወይም ሥርዓት የተለየ ሆኖ የምናገኘው በኦርቶደክስ ቤተ ክርስቲያን በየክብረ በዓላቱ ታቦቱ (ወይም ደግሞ ጽላቱ ታቦቱ አይወጣምና) የመውጣቱ ጉዳይ ነው ። ይህንን ሥርዓት በአይሁድ ሥርዓት ውስጥ ፈጽሞ አንመለከተውም ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይህንን በተመለከተ የምትሰጠው ምክንያት በብሉይ ኪዳን ጊዜ እሥራኤላውያን ወደ ጦርነት ሲሄዱ ታቦቱን አስከትለው ከመሄዳቸው ጋር በማመሳሰል ነው ። በተለይም የሚሰጠው ምሳሌ የኢያሪኮ ግምብ መፍረስ ታሪክ ነው ።

በእርግጥ ታቦቱ (እንዳለ እንጂ ጽላቱ ብቻ አይደለም) በጦርነት ጊዜ ከእግዚአብሔር ነቢይ ትዕዛዝ ሲያገኙ ይዘው ይወጡ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማንበብ ይቻላል ። የሆኖ ሆኖ በክብረ በዓል ጊዜ አንድም ቦታ አውጥተውት በዓሉን ሲያከብሩ ተጽፎ አናገኝም ። እንዲያውም አባ ኪዳነ ማሪያም ሲጽፉ “... ነገር ግን በክብረ በዓል ቀን

ታቦትን ይውጣ የሚል ትዕዛዝ በመጽሐፍ ቅዱስ አይገኝም ስለዚህ ነገር የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሚሰጡት ምክንያት ኢያሱ ኢያሪኮን ባፈረሰ ጊዜ ታቦተ ጽዮንን አሸክሞ ኢያሪኮን 7 ጊዜ ዞሯታል የሚል ነው ። ይህ ሕግም ትዕዛዝም አይደለም ሊሆንም አይችልም ። ታቦት የአምልኮታችን መግለጫ እንደመሆኑ መጠን በስደትና በዘመቻ ጊዜ ካጠገባችን ሊርቅ አይገባም ይኸውም እሥራኤል በኢያሱ ጊዜና በዔሊ ዘመን ያደረጉት እንደነበር ማለት ነው ። ... የኢትዮጵያ ነገሥታትም ይህን መሠረት አድርገው ወደ ጦር ሜዳ በሚጓዙበት ጊዜ ታቦትን እያሸከሙ ሲወሩና ሲዘምቱ ኖረዋል ። ይህም አድርጎታቸው ሁል ጊዜ የድል አክሊልን ሲያቀዳጃቸው ኖሯል ይሁን እንጂ በሰላም ጊዜ በክብረ በዓል ቀን በዓሉ ብቻ በሚገባ ተከብሮ ታቦት ባይወጣ የተሻለ ነው እላለሁ ። ምክንያቱም በሁሉም ዘንድ ግልጽ ስለሆነ መዘርዘር አያስፈልግም" ብለዋል ።

6ኛ) በመጨረሻ ሊጠቀስ የሚችለው ሌላው ልዩነት በብሉይ ኪዳን የነበረውን ሥርዓት በምናጤንበት ጊዜ (በመጽሐፉ መጀመሪያ በሰፊው እንደተመለከትነው) ከታቦቱ ጋር አብሮ የነበሩ ሌሎች የአምልኮት ቁሳቁሶች አለመኖራቸውና በታቦቱ ዙሪያ ይደረጉ የነበሩት ሥርዓቶች መቅረታቸው ነው ።

በእርግጥ ወደ ታቦቱ ሊቀርብ የሚችለው ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር ፥ የሚቀርበውም በዓመት አንድ ጊዜ የኃጢአት ማስተሰሪያ ደም ይዞ በታቦቱ ላይ በመርጨት ሥርዓቱን ያሳርግ ነበር ። ዛሬ ግን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በታቦቱ ዙሪያ ይህ ሥርዓት አይከናወንም ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ደሙን ስላፈሰሰና ለኛ መስዋዕት ስለሆነ የእርሱ ደም የሚፈተትበት የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ማስፈጸሚያ ሆነ ።

እንግዲህ ባጭሩ የሁለቱን የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን የታቦት ሥርዓት ለማገናዘብ ያስችለን ዘንድ ልዩነታቸውን ለመመልከት ሞክረናል ። አንዳንዶቹ ልዩነቶች መልስ ወይም በቂ መግለጫ የላቸውም አንዳንዶቹ መግለጫ አላቸው ነገር ግን የሚያረኩ ለመሆናችው ያጠራጥራል ።

ከዚህ በተጨማሪ African Zion የተሰኘ መጽሐፍ ስለ ታቦት ያሰፈረውን መመልከቱ ተጨማሪ ሃሳብ ሊያስገኝ ይችላል ። ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያን ቅዱሳት ሥዕሎችና የቅርጻ ቅርጽ ባህል ኤግዚቢሽን እአአ 1994 በአሜሪካ በተካሄደበት ጊዜ የታተመ ሲሆን በዚያ ኤግዚቢሽን ከቀረቡት ቅርጻ ቅርጾች መካከል አንድ መንበረ ታቦት ነበር ። ይህ መንበር 53 ሳንቲም በ23.5 ሳንቲም የሆነ



ከእንጨት የተሠራ በተለያዩ ቅርጻ ቅርጽ ያሸበረቀ ነው ። ይህ መንበር እንደ አዋቂዎቹ ግምት በ13ኛው ክፍለ ዘመን የተቀረጸ ነው ። የመንበሩ ጥቅም በውስጡ ጽላት ማስቀመጫ ሲሆን በስዕሉ ለመመልከት እንደሚቻለው በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን ጽላት ለማስቀመጥ የሚያንስ እንደሆነና በብሉይ ኪዳን ጊዜ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በሙሴ ከተሰራው የጽላቱ ማደሪያ ታቦት ጋርም ምንም ተመሳሳይነት እንደሌለው ለመረዳት ይቻላል ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካሄደው የታቦት (የቅዱስ ቅርባን) ሥርዓት ሚስጥራዊ ስለሆነና ከተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በስተቀረ ማንም ሊያገለግል ስለማይችል የጽላቱ ስፋትና ርዝመት ፥ ጽላቱ የሚቀመጥበት መንበረ ታቦት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ አጠራር ታቦቱ (ቤቤተ ክርስቲያኑ የሚገኝከሆነ) ምን እንደሚመስል፥ በውስጡ አንድ ወይም ሁለት ጽላት ይኑርበት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው ።

ይህ በስዕሉ ላይ የተመለከተው መንበረ ታቦት በ13ኛው ክፍለ ዘመን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ እንደዚሁም አሁንም በቤተ ክርስቲያኒቱ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ በሙሴ ጊዜ ከነበረው የጽላቱ ማደሪያ ከታቦቱ ጋር ዓይነተኛ ልዩነት እንደሚያሳይ ግልጽ ነው ።

ይህን ያህል ልዩነት መኖሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ሥርዓተ ታቦት ከቃል ኪዳኑ ታቦትና ከአይሁድ ሥርዓት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው ያመለክታል ። ይህንን አቋም ሬድሪክ ግሪዩስን እና ስትአርት ሙንሮ-ሄይ በመጽሐፋቸው አመልክተዋል ።

በእነርሱ አመለካከት በኢትዮጵያ የሚከናወነው ሥርዓት ከታቦት (ጽላቶቹ ከሚቀመጡበት) ጋር ሳይሆን ይልቅስ ከጽላት ጋር ነው ። በአገሪቱ በአክሱምና በሌሎች ከተሞች ተመላልሰው ባደረጉት ምርምርና ከቄሶች ፥ ከደብተራዎች እና ከመጻሕፍት ባገኟቸው መረጃዎች መሠረት ጽላት እንጂ ታቦት እንደሌለ ደምድመዋል ።

እነዘሁ ጸሐፊዎች በዚህ መጽሐፋቸው በስምንተኛው እና በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ከአርመን የመጡ ጎብኝዎች ታቦቱን ለማየት እንደቻሉ እና ይህ ያዩት ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው ታቦት ጋር በምንም ዓይነት እንደማይመሳሰል አመልክተዋል ።

በመጀመሪያ የተጠቀሱት በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያን የጎበኙት ዮሐንስ ቶቨማካን የተሰኙ አርመናዊ ነጋዴ ናቸው ። እኝህ ነጋዴ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ለንጉሣዊ ቤተሰብ ጌጣጌጥ ለመሸጥ ነበር ። ከዚያም እኤአ በ1764 ዓ ም ገደማ ወደ አክሱም ተጉዘው

በዚያም "ጽላተ ሙሴን" ለማየት እንደቻሉ ዘግበዋል ። ይህም በረከት ባሉ አልባሳት የተጠቀለለ በላዩ ጽሑፍ የሰፈረበት የእንጨት ጽላት እንደነበረ ጽፈዋል ። እዚህ ላይ ትክክለኛውን ጽላተ ሙሴ አሳይተዋቸው ከነበረ በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሰው ጽላተ ሙሴ ጋር ልዩነት መፍጠሩ ግልጽ ይሆናል ። ጽላተ ሙሴ ከድንጋይ የተቀረጸ ነበርና ። ነገር ግን ይህንን የመሰለ በአገሪቱ ትልቅ ክብር የሚሰጠውን የአምልኮት ዕቃ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለአንድ የውጭ አገር ዜጋ እንዲህ በቀላሉ አሳይተው ነበር ብሎ ለመገመት የሚያስቸግር ይሆናል ።

ሌላኛው አርመናዊ ጎብኚ አባ ዲሞቴዎስ ቫርታቤት ሳፑሪትቻን የተባሉት ሲሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ነበር ። እኚህ የሃይማኖት አባት የኢየሩሳሌም ፓትሪያርክንና ልዑካኖች ጋር አብረው የመጡ ነበሩ ። ይህ ልዑካን በመቅደላ በንጉሡ ትዕዛዝ ታሥረው የነበሩትን እንግሊዞች የሚለቀቁበትን መንገድ ለመፈለግ የተላከ ነበር ። እኚህ አባት እኤአ ግንቦት 1869 ዓም በጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን በላዩ አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፈበትን ጽላት ለማየት ተፈቅዶላችው እንደነበር ዘግበዋል ። ይህንን ዕድል የፈቀዱላቸው ከብዙ ክርክርና ድርድር በኋላ በዚያን ጊዜ በደጃዝማችነት ማዕረግ የነበሩት በኋላም ዓፄ ዮሐንስ አራተኛ ተብለው በነገሡት በደጃች ካሣ ፈቃድ እንደነበር ዘግበዋል ። የተመለከቱትን ጽላት ሲገልጹ " ከቀይ እምነበረድ የታነጸ ፥ ቁመቱ 24 ሳንቲም ፥ ስፋቱ 22 ሳንቲምና ውፍረቱ ደግሞ 3 ሳንቲም የሆነ ፥ በላዩ ደግሞ አሥርቱ ትዕዛዛት ተጽፎበት እንደነበረም አመልክተዋል ። ይህንን ከተመለከቱ በኋላ አባ ዲሞቴዎስ ይህ የሙሴ ጽላት እንዳለሆነ በሁለት ምክንያቶች ለማረጋገጥ እንደቻሉም አስፍረዋል ። አንደኛው በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፉት በሁለት እንጂ በአንድ ጽላት ብቻ እንዳልነበረ ፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ትዕዛዛቱ የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ እንጂ በግዕዝ እንዳልነበረ ነው ።

የኚህም የሃይማኖት አባት ዘገባ ከእርሳቸው ቀደም ብለው እንደመጡት እና ጽላቱን አይቻለሁ በለው እንደዘገቡት አርመናዊ ነጋዴ በተመሳሳይ ሁኔታ ለመቀበል ያስቸግር ይሆናል ። አንድ ነገር ግን ግልጽ ሆኖ ይታያል በሁለቱም ሥፍራ ፥ በሁለቱም ዘገባዎች የሚጠቀሰው ጽላት እንጂ የጽላቱ ማደሪያ ታቦት እንዳልሆነ ነው ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አቡ ሳሊህ የተሰኙ ጸሐፊ " የግብጽና የጎረቤት አገሮች አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት " በተሰኘው

መጽሐፋቸው በኢትዮጵያኖች ዘንድ የዳዊት ዙፋንና የቃል ኪዳኑ ታቦት እንድሚገኝ ካሰወሱ በኋላ የቃል ኪዳኑን ታቦት በዝርዝር ሲገልጹት "... በውስጡ በእሥራኤል ልጆች ላይ የተደነገጉት ትዕዛዛት በእግዚአብሔር እጅ የተጻፈባቸው ሁለት ጽላቶች ይገኛሉ :: ታቦቱ የመሰውያውን ያህል አይተልቅም :: ቁመቱ እስከ ሰው ጉልበት ድረስ ይደርሳል :: በወርቅ ደግሞ ተለብጧል :: በመከደኛው ላይ በወርቅ የተሠሩ መስቀሎች እና አምስት የከበሩ ፈርጦች አሉበት" ብለው አስፍረዋል :: ከዚህ በተጨማሪ በታቦቱ ዙሪያ በዓመት አራት ጊዜ ሥርዓተ አምልኮት እንደሚፈጸም ፥ በሥርዓቱ ጊዜም ታቦቱን የሚሸከሙት ከዳዊት ዘር የሆኑ ቀያይ እሥራኤላውያን እንደነበሩም ይዘግባሉ ::

አሁንም ይህንን ዘገባ ለመቀበል የሚያስቸግር ይሆናል :: በአቡ ሳሊህ አገላለጽ የምንመለከተው ታቦት እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከታነጸው ታቦትጋር ትልቅ ልዩነት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን:: አንደኛ በዚህ አገላለጽ መሠረት ታቦቱ በመስቀል ያጌጠ ነው :: ይህ ከክርስትና ጋር እንጂ ከአይሁድ ሥርዓት ጋር ግንኙነት እንደሌለው ያሳያል :: በመከደኛው ላይ መገኘት የነበረባቸው ሁለት ኪሩቤሎች ደግሞ አልተገለጹም :: ይህ በአቡ ሳሊህ የተገለጸው ታቦት በክርስቲያኖች የታነጸ መሆን አለበት !!

እስካሁን ስንመለከተው የነበረው የቃል ኪዳኑ ታቦት በቤተ መቀድስ ሥርዓትና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያለውን ልዩነት ነበር :: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ እንደ ሮድሪክ ግሪዩሰን እና እንደ ስተአርት ሙንሮ-ሄይ አመለካከት በመጀመሪያ ታቦት ከአረቦች ቀጥሎም ከእስልምና እምነት ጋር ቅርበት አለው ብለው የዘገቡትን ለመዳሰስ እንሞክራለን::

አይሁዶች በአረቢያ በተለይም በየመን አካባቢ ይገኛሉ :: እንዲያውም እነዚህ አይሁዶች ትክክለኛ የእሥራኤል ዜጎች መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የዲ ኤን ኤ (DNA) ምርመራ እንደተደረገላቸው የኢትዮጵያውያን አይሁዶች (ፈላሻን) በሚመለከት በተዘጋጀ ኮንፈረንስ ላይ ሲነገር ሰምቻለሁ ::

በዚያ በአረቢያ በሚገኙት አይሁዶች ዘንድ የሚታወቀው አፈ ታሪክ የአይሁድ ሃይማኖትና አይሁዶች እራሳቸው ወደዚህ የዓለም ክፍል ሊመጡ የቻሉት የየመን/የአረቢያ ንግሥት የነበረችው ንግሥት ሳባ ንጉሥ ሰለሞንን በኢየሩሳሌም ጎብኝታ ከተመለሰች በኋላ እንደነበረ ነው :: ሁለቱ በተገናኙበት ጊዜ ያፈሩት ልጃቸው በደቡብ አረቢያ በአይሁድ ሥርዓት እንዳደገም ይነገራል :: ንጉሥ ሰለሞን የልጁን

ትምህርትና ዕድገት እንዲከታተሉ የላካቸው እሥራኤላውያን ሰነዓ በተባለችው ከተማ እንደሰፈሩም ይነገራል ። የኢትዮጵያ ንጉሥ ካሌብ ክርስቲያኖችን በመደገፍ ወደ አረቢያ ዘምቶ አካባቢውን የተቆጣጠረው በዚያ ይኖሩ በነበሩ ክርስቲያኖች እና አይሁዶች መካከል የተነሳውን ግጭት ለመግታት እንደነበር ታሪክ ይዘግባል ።

ዋሂብ ኢብንሙናቢ የተባሉ የታሪክ ሊቅ "ኪታብ አል ቲጃን" በተሰኘ መጽሐፋቸው እሥራኤላውያን ከዳዊት እና ከሰለሞን ዘመነ መንግሥት በኋላ የቃል ኪዳኑ ታቦት በእጃቸው እንደነበረ ፣ ከዚያም በእነርሱና የመካን አካባቢ ይቆጣጠሩ በነበሩ "ጁርሁማውያን" በሚባሉ ጎሳዎች መካከል ጦርነት ተካሄዶ እሥራኤላውያን ሲሸነፉ ታቦቱ እንደተማረከባቸው ከዚያም የነዚህ "ጁርሁማውያን" እንደወሰዱት ዘግበዋል ።

ሌላም አል ሃምዳኒ የተባሉ ሊቅ ይህንኑ ታሪክበማሻሻል የቃልኪዳኑ ታቦት ወደ መካ ተማርኮ "ጁርሁማውያን" በወሰዱት ጊዜ ወደ ሁለት ሞተ ሺህ ሕዝብ እንዳለቀ ጽፈዋል ። ይህ ብቻ አይደለም የቃል ኪዳኑ ታቦት በአረቦች ዘንድ ለመገኘቱ የእስልምና መጽሐፈ እምነት "ቁርዓን" በሁለተኛው ሱራ ላይ "ነቢያቸው እንዲህ አላቸው እነሆ! የመንግሥቱ ምልክት ታቦቱ ወደእናንተ መምጣቱ ነው ..... በዚህም ካመናችሁ ለእናንተ ምልክት ይሆናል" ይላል ።

በመጨረሻም ከሰባ ዓመታት በፊት በሰሜን አረቢያ ያደረጉትን ጉብኝትና ምርምር የዘገቡት አስትራሊያዊው ካርል ራስዋን ሩአላ ተብለው በሚጠሩ ጎሳዎች ዘንድ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ሥርዓት እና አገልግሎት ጋር በቅርብ የሚመሳሰል የአምልኮ ዕቃ እንዳለ ጠቅሰዋል። ይኸው ዕቃ በግመል ላይ የሚቀመጥ ሲሆን የሚሠራውም ከወይራ እንጨት ሆኖ በሰጎን ላባ የተሸፈነ ነው ። ስሙንም "አቡ ዱሁር" ብለው ይጠሩታል ። በአቡ ዱሁሩና በቃል ኪዳኑ ታቦት ያለው ተመሳሳይነት እንደሚከተለው ነው ፤

- የመንገዳቸውን አቅጣጫ የሚወስን/የሚያመለከት ነው ፤
- በበረሃ ውስ፤
- በጉዞዋቸው ሲመሽባቸው የሚያርፉበትን ሥፍራ የሚወስን ነው ፤ (ከእሥራኤላውያን የበረሃ ጉዞ ጋር የተመሳሰለ ነው)
- ወደ ጦርነት የሚመራቸውና በጠላቶቻቸው ላይ ድልን የሚያቀዳጃቸው ነው ፤
- በመጨረሻም የአምላካቸው ማደሪያ ነው ።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ነጥቦች ፤ ማለትም አይሁዳውያን በአረቢያ ውስጥ መገኘታቸው ፥ ከቃል ኪዳኑ ጋር የተያያዘ ታሪኮች

መኖራቸው ፥ አልፎ ተርፎም የቃል ኪዳኑ በቁርዓን ውስጥ መጠቀሱ እና ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር በቅርብ የሚመሳሰል የአምልኮ ሥርዓት መገኘቱ አንደኛ ንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊት አይደለችም የአረቢያ/የየመን ተወላጅ ናት የሚለውን አመለካከት የሚያጠናክር ፥ ሁለተኛ ደግሞ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ሳይሆን ወደ አረቢያ ነው የመጣው በማለት በኢትዮጵያውያኖች ለረዥም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ታሪክ የሚያፈርሰው ይሆን?